## በቪክቶሪያ ትምህርትና ስልጠና አሰጣጥ ስርዓት ማወቅ

# Understanding the Victorian Education & Training System

# አዲስ ለመጡ ወጣቶች መመሪያ

## ሁለተኛ እትም

### ከተለያየ ባህልና ቋንቋ ለመጡ ወጣቶች የሚያስፈልግ መረጃዎችን ለማሟላት ሲባል በዚህ ትንሽ መጽሐፍ ተዘጋጅቷል።

በስደተኛ ወጣቶችና የመሸጋገሪያ የሥራ ቡድን ከሁለገብ ባህላዊ የወጣቶች ጉዳይ ማእከል/ Refugee Young People and Transitions Working Group በጋራ በ2003 ዓ.ም የተዘጋጀ ነው።

**አዲስ ለመጡ ወጣቶች መመሪያ በሁለገብ ባህላዊ የወጣቶች ጉዳይ ማእከል/** Centre for Multicultural Youth Issues **የተዘጋጀ ሲሆን በኢሚግሬሽን፣ ሁለገብ ባህላዊ እንዲሁም የአገሬቱ ባላባቶች ጉዳይ መምሪያ/**DIMIA **የገንዘብ እርዳታ ሲያቀርብ ለመጀመሪያ ጊዜ በ**1998 **ዓ.ም ለሕትመት ቀርቧል።**

**በዚሕ ወቅት የወጣው ጽሁፍ በቪክቶሪያ የሰፈራ ዕቅድ ኮሚቴ፣ ለስደተኛ ወጣቶች መሸጋገሪያ የሥራ ቡድን/ Victorian Settlement Planning Committee's Refugee Young People and Transitions Working Group ከወጣቶች ጉዳይ ማእከል/ Centre for Multicultural Youth Issues ጋር በመሆን ሕትመቱ ወቅታዊ ሆኖ የቀረበ ይሆናል።**

**ይህ ሰነድ ሲወጣ አስተዋጽኦ ላደረጉ ወኪሎችና ሌሎች የከበረ አድንቆት ይገባቸዋል። በነዚህ ወኪሎች ውስጥ የቪክቶሪያ እንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት ቤት እከላት፣ የአዋቂ ማይግሬንት እንግሊዝኛ ፕሮግራም/** AMEP **ለሚያቀርቡ፣ የሁለተኛ ደረጃ ኮሌጆች፣** TAFE **እና ዩኒቨርሲቲዎችን ያጠቃለለ ይሆናል።**

**በስደተኛ ወጣቶች የመሸጋገሪያ የሥራ ቡድን ወኪሎች አባላት የሚጠቃለል የኮመን ዌልዝ አውስትራሊያ፣ የራሱ ኃላፊዎች፣ ሠራተኞችና ወኪሎች ወይም በሕትመቱ ላይ ባለው መረጃ ተመርኩዞ በቸልተኝነት ወይም በሌላ ምክንያት ለሚከሰት ጉድለት ተጠያቂ አያደርጋቸውም።**

(c) 2003 by the Centre for Multicultural Youth Issues

**Centre for Multicultural Youth Issues**
Level1, 308 Drummond Street
CARLTON VIC 3053

**Victorian Settlement Planning Committee, Secretariat**
Department of Immigration and Multicultural and Indigenous Affairs
Level 25 Casselden Place, 2 Lonsdale Street
MELBOURNE VIC 3000

Phone: (03) 9235 3357 Fax: (03) 9235 3266
Email: nicholas.chiam@immi.gov.au

**መግቢያ** ... **5**

**በቪክቶሪያ ትምህርት ስርዓት** ... 6

**በአውስትራሊያ ሙያ ኣሠራር** /Australian Qualification Framework ... **7**

*በቪክቶሪያ የትምህርና ስልጠና አሰጣጥዳ* ... *7*

**የእንግሊዝኛ ቋንቋ ት/ቤት ማእከላት** /English Language Schools and Centres ... 8

*አዲስ ለመጡ ፕሮግራም* ... *8*
*ከደረሱ በኋላ የሚሰጥ ፕሮግራም* ... *8*
*የበለጠ ማብራሪያ እንዴት ማግኘት እንደሚቻል?* ... *9*

**በቪክቶሪያ የአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት** ... 10

*የት/ቤት እውነታዎች* ... *10*
*ስርዓተ ትምህርት* ... *10*

**በቪክቶሪያ ትምህርት የምስክር ወረቀት** /Victorian Certificate of Education ... 11

*VCE ማለት ምንድ'ነው?* ... *11*
*VCE እንዴት ይቀርባል?* ... *11*
*VCE VET [የሥራ፥ ትምህርትና ስልጠና]* ... *11*
*እንግሊዝኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋEnglish as a Second Language* ... *12*
*VCE እንዴት እንደሚገመገም?* ... *12*
*ለአገር አቀፍ ሶስተኛ ደረጃ ማስገቢያ የሚተካ የመመዘኛ (ENTER) ነጥብ* ... *13*
*ወደ ትምህርት ለሚመለሱ ተማሪዎች [አዋቂ ተማሪዎች]* ... *13*
*በሌላ አገር የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ጨርሰዋል'ወይ?* ... *13*
*ከVCE ትምህርትህ ጋር በዩኒቨርሲቲ ውስጥ የትምህርት ዓይነት መውሰድ* ... *13*
*የበለጠ ማብራሪያ እንዴት ማግኘት እንደሚቻል?* ... *13*

**በቪክቶሪያ ተግባራዊ ትምህርት የምስክር ወረቀት** /(VCAL) ... 14

*VCAL ምን ማለት ነው?* ... *14*
*VCAL መውሰድ የሚችል ማን ነው?* ... *14*
*ለመግቢያ የሚያስፈልጉ ነገሮች* ... *14*
*VCAL ለመጨረስ ምን ያህል ጊዜ ይወስዳል?* ... *14*
*VCAL የት ነው የማካሂደው?* ... *14*
*በVCAL በኩል ምን ዓይነት ትምህርት ይወሰዳል?* ... *15*
*VCAL እንዴት ይገመገማል?* ... *15*
*VCAL በመውሰድ ምን ዓይነት ነጥብ/ማእረግ ይሰጣል?* ... *15*
*በትርፍ ሰዓት መሥራት ይቻላል እንዲሁም/ወይም እየሠሩ በVCAL በኩል ትምህርት ለመውሰድ መመዝገብ ይቻላል ወይ?* ... *16*
*VCAL ከወሰዱ በኋላ ምን እንደሚገኝ?* ... *16*
*VCAL ከወሰዱ በኋላ የት መሄድ እንደሚፈልጉ?* ... *16*
*ለበለጠ ማብራሪያ እንዴት ማግኘት እንደሚቻል?* ... *16*

**AMEP ናይ እንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል** /AMEP English Language Classes ... 17

*በAMEP ፕሮግራም ማን ነው የሚማር?* ... *17*
*AMEP ፕሮግራም ለመማር የሚቻልበት መንገድ፡* ... *17*
*በAMEP ፕሮግራም የተሳተፉና ማግኘት የሚችሉት፡* ... *17*

*በበለጠ የእንግሊዝኛ ክፍሎችን ለመሳተፍ የሚቻልበት መንገድ....18*
*የበለጠ ማብራሪያ እንዴት ማግኘት እንደሚቻል?....18*
*ቋንቋ፣ የማንበብና መጻፍ እንዲሁም የቁጥር ትምህርት ፕሮግራም/(LLNP)....18*

**የሙያና ተጨማሪ ትምህርት**/(TAFE)....20

*ሙያዎች....20*
*የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት....21*
*ለ TAFE ተቋማት መግቢያ....21*
*ዩኒቨርሲቲ ለመግባት የTAFE አስፈላጊነት....22*
*ለትምህርት ክፍሎች ክፍያ....22*
*ለበለጠ ማብራሪያ እንዴት ማግኘት እንደሚቻል?....22*

**የኒቨርሲቲዎች**....23

*አነስተኛ የመግቢያ ነጥብ....23*
*ልዩ የሆነ የመግቢያ እድል ማግኘት....23*
*የVCE ትምህርት ለጨረሱ ተማሪዎች የሚያስፈልግ ኮርስ....24*
*በቪክቶሪያ የሶስተኛ ደረጃ ኮርሶችን ለማግኘት እንዴት ማመልከቻ እንደሚገባ....24*
*ከፍተኛ የትምህርት አስተዋጽኦ አሠራር (HECS)....24*
*ለበለጠ ማብራሪያ እንዴት ማግኘት እንደሚቻል?....24*

**ለገቢ ምንጭ እርዳታ**....26

*ለወጣቶች የሚሰጥ አበል/ክፍያ....26*
*ለተማሪዎች የሚሰጥ አበል....26*
*ልዩ የጥቅም ክፍያ....26*
*በገቢ መጠንና በንብረት ግምገማ....26*
*ነዋሪነት....27*
*ተጨማሪ ጥቅም ያለው....27*
*ለወጣቶች በሴንተርሊንክ አገልግሎት....28*
*ለሴንተርሊንክ የሚደረግ ጊዜታ....28*

**የበለጠ ማብራሪያ የሚገኝበት ምንጮች**....29

*አጠቃላይ መረጃዎች....29*
*ለ VCE/VCAL አጠቃላይ ማብራሪያ....29*
*ስለ ርቀት ትምህርት መረጃ....29*
*ለወላጆች አጠቃላይ የትምህርት መረጃ....29*
*ስለ TAFE መረጃ....29*
*ስለ ሥራ፣ TAFE እንዲሁም ዩኒቨርሲቲ መረጃ....29*

# መግቢያ

በአውስትራሊያ ለመማርና ለመሰልጠን ለሚፈልጉ ስደተኛና በቅርቡ ለመጡ ወጣቶች አስፈላጊ የሆነ መረጃ በዚህ ትንሽ መጽሐፍ ውስጥ ቀርቧል።

በቅርቡ ለመጡ ወጣት ስደተኞች ስለ አጠቃላይ የቪክቶሪያ ትምህርታዊና ስልጠና አሰራር አስፈላጊ ነገሮችን ይረዳ ዘንድ ለማወቅ ይህ ትንሽ መጽሐፍ ተዘጋጅቷል። ብዙ ዓይነት የትምህርትና ስልጠና እድል እያለ ነገር ግን ባለማወቅ ሰዎች በየኮርሱ የሚያስገባ ግልጽ የሆነ የመረጃ መንገድ ስለሚያጥራቸው ግልጽ መረጃ እንዲያገኙ ታስቦ የተዘጋጀ ነው።

የመሸጋገሪያ መንገድ/Pathways በቪክቶሪያ ትምህርታዊና ስልጠና አሰራር የሚቀርቡትን ደረጃዎች ለመግለጽ የቀረበ አነጋገር ይሆናል። የትኛውን ኮርስ መውሰድ እንዳለብዎ በነዚሕ የደረጃ አመራረጥ ይቀርባሉ። በጥንቃቄ የተመረጠ የመሸጋገሪያ መንገድ/Pathways አንድ ሰው የሥራ እቅዱንና ፍላጎቱን እንዲያሟላ ሲያደርግ በወቅቱ ያላቸውን የእንግሊዝኛ ደረጃና የቋንቋ አስፈላጊነት በመገንዘብ የሚመረጠው የትምህርትና ስልጠና እድል መመሳሰሉን ለማጤን ይሆናል።

እንግሊዝኛ ቋንቋ የሚያስፈልጋቸው ብዙ ወጣቶች በቅድሚያ አዲስ ለመጡ የሚሰጥ የእንግሊዝኛ ፕሮግራም መመዝገብ አለባቸው። ብዙ ጊዜ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ት/ቤት ወይም ማእከል [እድሚያቸው እስከ 18 ዓመት ከሆኑ] ወይም በAMEP እድሚያቸው ከ18 ዓመት በላይ ለሆኑ] ወጣቶች ይቀርባል።

ወጣቶች ለእንግዳ የሚቀርበውን የእንግሊዝኛ ፕሮግራም ሲጨርሱ ከዚያ በላይ የትምህርት ሥልጠና መውሰድ ለሚፈልጉ እና ትክክለኛ የሆነው ኮርስ የት እንደሚገኝ ለማወቅ እንደሚቸገሩ ነው። ሰዎች ለወደፊት ማድረግ ያለባቸውን በቅድሚያ ለማወቅ እንዲያውቁ በዚህ ትንሽ መጽሐፍ አማካኝነት ማብራሪያና ምክር ለመስጠት ታቅዶ ነው።

እንደዚህ ዓይነት የመጀመሪያ ደረጃ መሸጋገሪያ መንገድ/Pathways ከእንግዳ እንግሊዝኛ ኮርስ ወደ የእንግሊዝኛ ቋንቋና ሥራ ወይም በተለይ ወደ ሥራ የሚመራ የሙያ ስልጠና ትምህርት ሊመራ ይችላል። ሁለተኛ ደረጃ የመሸጋገሪያ መንገድ/Pathway ደግሞ ከእንግዳ እንግሊዝኛ ኮርስ በቀጥታ ወደ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ወይም ከዚያ በላይ ትምህርት ደረጃ ሊመራ ይችላል።

ከግዴታዊ ት/ቤት ስርዓት ወደ ዩኒቨርሲቲ በመኼድ የፕሮፌሽናል ሙያ ወይም በሥራ ሙያ ለመማር የሚደረግ የመሸጋገሪያ መንገድ/Pathway ብቻ አይደለም። ኣዲስ የመጡ ወጣቶች በቂ የሆነ መደበኛ የእንግሊዝኛ ችሎታ እንዲያገኙ፤ በአውስትራሊያ ትምህርት ስርዓትና በአገራቸው የነበራቸው ትምህርት ተቋርጦባቸው ለነበረ ወጣቶች ትምህርታቸውን እንደገና ለማደስ ተጨማሪ ጊዜ እንደሚፈልጉ ነው። በዚህ ዓይነት ለማካኼድ የታቀደ አንዳንድ የመሸጋገሪያ መንገድ/Pathway እንዳለ ነው። አዲስ ማይግራንትና ስደተኛ ወጣቶች አገባብ ባለው መንገድ እንዲከተሉና እንዳይበሳጩ ለማድረግ ሕጋዊ የሆኑ አማራጭ የመሸጋገሪያ መንገዶች/Pathways እንዳሉ ማሳወቅ አስፈላጊ ይሆናል።።

ለተለያዩ ሰዎች የተለያየ የተለያየ የመሸጋገሪያ መንገዶች/Pathways እንዳሉና ጠቃሚ በሆኑት መረጃዎች ላይ ማተኮር ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ይሆናል። በአውስትራሊያ ጥሩ ትምህርት ወይም ስልጠና ለመጀመር እድል እንድታገኙ የመሸጋገሪያ መንገድ/Pathway በዚህ ትንሽ መጽሐፍ ውስጥ መረጃ እንደምታገኙ ተስፋ እናደርጋለን።

# በቪክቶሪያ የትምህርት ስርዓት



# በአውስትራሊያ ሙያ ኣሠራር

## *በቪክቶሪያ የትምህርትና ስልጠና አሠራር*

| ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት | በቪክቶሪያ የሥራና ስልጠና የምስክር ወረቀት (VET) [TAFE እንዲሁም ሌሎች የታወቁ አገልግሎቶች የሚያቀርቡ] | ከፍተኛ ትምህርት [ዩኒቨርሲቲዎች] |
|---|---|---|
| ➢ [10ኛ]፣ 11ኛና 12ኛ ክፍል በቪክቶሪያ ትምህርት የምስክር ወረቀት (VCE) [በቪክቶሪያ የሥራና ስልጠና ምስክር ወረቀት (VET) የሚል ያተቃለለ ይሆናል] ወይም<br>➢ በቪክቶሪያ ተግባራዊ ትምህርት የምስክር ወረቀት (VCAL) ወይም<br>➢ የአህጉራዊ Baccalaureate (IB) | ➢ ምስክር ወረቀት I<br>➢ ምስክር ወረቀት I I [እንደ ትሬኒሽፕ ተመሳሳይ] | |
| | ➢ ምስክር ወረቀት II [ከምስክር ወረቀት የበለጠ ወይም ከዲፕሎማ ጋረ የተቀራረበ]<br>➢ ዲፕሎማ<br>➢ ከዲፕሎማ የላቀ | ➢ ዲፕሎማ<br>➢ ከዲፕሎማ የላቀ |
| | ➢ የመጀመሪያ ዲግሪ | ➢ የመጀመሪያ ዲግሪ<br>➢ የድሕረ ዲግሪ ምስክር ወረቀት<br>➢ የድሕረ ዲፕሎማ<br>➢ ማስተር ዲግሪ<br>➢ የዶክትሬት ዲግሪ |

# የእንግሊዝኛ ቋንቋ ት/ቤትና ማእከላት

## አዲስ ለመጡ ፕሮግራም New Arrivals Program

አዲስ ለመጡ ተማሮዎች እንግሊዝኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ (ESL) እንዲማሩ የሚፈቀድላቸው በአዲስ ለመጡ በሚለው ፕሮግራም ሲሆን በነጻ በመንግሥት ት/ቤቶች የሙሉ ቀን ትምህርት ክፍሎች መከታተል ይችላሉ። ይህ ፕሮግራም ብዙ ጊዜ በአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ የእንግሊዝኛ ት/ቤቶችና እንግሊዝኛ ቋንቋ ማእከላት (ESL/Cs) በኩል ሲቀርብ እንዲሁም በጂሎንግ፣ ሸበርቶን የእንግሊዝኛ ፕሮግራሞች ይቀርባል።

የመኖሪያ ፈቃድ ያላቸውና በአውስትራሊያ ከ6 ወራት በታች ለቆዩ እንዲሁም በአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የጀመሩትን ኮርስ ለመጨረስ ለሚፈልጉና ትምህርት በእንግሊዝኛ ቋንቋ ት/ቤት-ማእኸል ፕሮግራም ይቀርባል። የጊዚያዊ መኖሪያ ቪዛ ያላቸው ለአንዳንድ ተማሪዎች ክፍት ቦታ ካለ ሊማሩ ይችላሉ። ከጥር/January 1 ቀን ጀምሮ እድሚያቸው ከ18 ዓመት በላይ ለሆኑ ተማሪዎች መመዝገብ አይፈቀድላቸውም ይሁን እንጂ ለነርሱ የሚጠቅም ፕሮግራም ማለት እንደ አዋቂ ማይግራንት የእንግሊዝኛ ፕሮግራም (AMEP) ወይም TAFE ኮርሶች እንደሚኖሩ ምክር ይሰጣል።

ብዙ ጊዜ አንድ ተማሪ ለሁለት ተርሞች/ፈረቃ [6 ወራት] ክፍል ይከታተላል። በሰብዓዊ ወይም ከስደት ዓለም ለመጡ ተማሪዎች ወይም ቀደም ሲል ትምህርታቸውን ላቋረጡ ተማሪዎች እስከ አንድ ዓመት ሊቆዩ ይችሉ ይሆናል።

በመደበኛ ስርዓተ ትምህርት መሠረት ለሚከታተሉ ተማሪዎች ተጨማሪ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ፕሮግራም በእንግሊዝኛ ቋንቋ ት/ቤት-/ማእኸል በኩል ፕሮግራም ይቀርባል። ተማሪዎች በአውስትራሊያ የመደበኛ ት/ቤት ሲከታተሉ የእንግሊዝኛ ችሎታቸውን ለማስተካከል ሲባል የታቀደ ፕሮግራም ነው። ለተማሪዎች የሚረዱ እንዲሁም በወላጆችና ት/ቤት መካከል ጠንካራ ግንኙነት እንዲኖር በብዙ ባህሎች ለመማር የሚረዱ ሰዎች (MEALs) ይቀጠራሉ።

ተማሪዎች በእንግሊዝኛ ቋንቋ ት/ቤት-/ማእከል ወይም በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት በቀጥታ መመዝገብ ሲችሉ ወይም በሌላ ድርጅት ሊላኩ ይችላሉ። ተማሪዎች ምዝገባን በተመለከተ በአካባቢያቸው የሚገኘውን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ት/ቤት-/ማእከል መጠየቅ ይቻላል። የቋሚ መኖሪያ ፈቃድ ያላቸው ተማሪዎች በእንግሊዝኛ ቋንቋ ት/ቤት-/ማእከል ሲመዘገቡ የነጻ ትራንስፖርት ፈቃድ ያገኛሉ።

## ከደረሱ በኋላ ፕሮግራም

ተማሪዎች በእንግሊዝኛ ቋንቋ ት/ቤት ወይም ማእከል ከነበሩና ለአዲስ መጤ የሚሰጠው ኮርስ ሲያልቅ ወደ ሌላ የተሻለ ት/ቤት እንዲገቡ ድጋፍ ይደረግላቸዋል።

አንድ ወጣት በእንግሊዝኛ ቋንቋ ት/ቤት ወይም ማእከል ሲያጠናቀቁ ብዙዎቹ የ(ESL) ተማሪዎች ወደ መደበኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት በመግባት በበለጠ የእንግሊዝኛ ቋንቋ(ESL) እርዳታ እንዲያገኙ ይደረጋል። እንዲሁም እነዚህ ተማሪዎች በበለጠ ለሥራና ትምህርት እንዲዘጋጁ እርዳታ በበላይ ባሉ አካላት ይቀርብላቸዋል።

በአገራቸው እያሉ መጠነኛ ትምህርት የነበራቸው አንዳንድ ተማሪዎች ወደ አውስትራሊያ ሲገቡ ሥራ ለመፈለግ ሲሉ ትምህርታቸውን ያቋርጣሉ ወይም እንግሊዝኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው ESL ለሆነ ወጣቶች የሚገለገሉበት በTAFE ፕሮግራም ወይም ከአዋቂ መማክርት ትምህርት Adult Council of Education

## የበለጠ ማብራሪያ እንዴት ማግኘት እንደሚቻል?

የትምህርትና ስልጠና መምሪያ/ DE&T
አዲስ ለመጡ ዌብ ሳይት በቪክተሪያ ያሉ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ት/ቤት-/መእከላት
http://www.sofweb.vic.edu.au/lem/esl/enew.htm
ስልክ ቁጥር: (03) 9637 2131
ፋክስ ቁጥር: (03) 96372050

# በቪክቶሪያ የአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ስርዓተ ትምህርት

## ስለ ት/ቤት እውነታዎች

እድሜያቸው ከ6 እስከ 10 ዓመት ላሉ ሕፃናት በቪክቶሪያ ውስጥ የመማር ግዴታ አለባቸው። ተማሪዎች በጠቅላላው 13 ዓመታት የሚሆን በት/ቤት መከታተል ሲችሉ 7 ዓመታት የሚሆን በአንደኛ ደረጃ ት/ቤት [ለ6ኛ ክፍል ዝግጅት] እንዲሁም 6 ዓመታት በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት [ከ7ኛ እስከ 12ኛ ክፍል] መቆየት አለባቸው።

በቪክቶሪያ የተለያዩ ት/ቤቶች ይገኛሉ፡ አዚህም ትምህርታዊ፣ ለአንድ ጾታ ብቻ፣ ሃይማኖታዊ፣ የግልና የመንግሥት ት/ቤት ማካሄድ ይቻላል።

ት/ቤት በየዓመቱ በጥር/January መጨረሻ ጀምሮ በታህሳስ/December መጨረሻ ያበቃል። በአንድ ዓመት ውስጥ አራት ተርሞች ሲኖሩ በየተርም ፈረቃው ለሁለት ሳምንታት የሚሆን የእረፍት ጊዜ ይኖራል። ከታህሳስ/December ወር እስከ ጥር/January ጊዜ ረጅም የእረፍት ጊዜ ይኖራል። ት/ቤት ከሰኞ እስከ ዓርብ ከ9.00am እስከ 3.30pm ባለው ጊዜ ውስጥ ይካሄዳል።

## ስርዓተ ትምህርት

ተማሪዎች ለወደፊቱ የሥራ እድላቸው እንዲዘጋጁ አጠቃላይ የሆነ ስርዓተ ትምህርት በሁሉም የትምህርት መስክ ይሰጣል። ሰፋ ያለና በተለያየ የሙያ ትምህርታዊ ደረጃዎችን ያቀፈ ከዚህ በታች ባሉ የትምህርት መስኮች ስልጠና ለተማሪዎች ይቀርባል፡

- የኪነ-ጥበብ
- የእንግሊዝኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት
- የጤና ጥበቃና የአካል ጥንካሬ
- ከእንግሊዝኛ ባሻገር ሌላ ቋንቋ
- የሂሳብ ትምህርት
- የሳይንስ
- የሰብዓዊና ማሕበራዊ ሳይንስ
- የቴክኖሎጂ

በት/ቤት የሚገኘው የትምህርት ዓይነት ከስርዓተ ትምህርቱ ጋር መመሳሰል ይገባል፣ ይሁን እንጂ በየትምህርት መስኩ የተለያየ የትምህርት ዓይነት ይቀርባል። ተማሪዎች ለሥራ ሲዘጋጁ በፈለጉት መንገድ ት/ቤቱ እንዲሰለጥኑ ያደርጋል። በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የሙያ አስተማሪዎች ተማሪዎችን በፈለጉበት የሥራ መስክ እንዲመርጡ መመሪያ ያቀርባሉ። እንዲሁም የተማሪዎች በጎ አድራጎት አስተባባሪ ስለ ደህንነት ጉዳይ በተመለከተ ምክር በመስጠት ተማሪዎች ትምህርታቸውን በብቃት እንዲከታተሉ ይረዳሉ።

# በቪክቶሪያ ትምህርት የምስክር ወረቀት
# Victorian Certificate of Education

[ማስታወሻ፡ ከዚህ መግለጫ ወይም ማብራሪያ ለውጥ ሊኖረው ይችላል። ት/ቤቶችና አገልግሎት አቅራቢ አካሎች ስለ VCE ወቅታዊ የሆነ መረጃ ሲኖራቸው እንዲሁም በቪክቶቲያ ስርዓተ ትምህርና የገምጋም ባለሥልጣን (VCAA) በሚል ዌብ ሳይት http://www.vcaa.vic.edu.au መጎብኘት ይሆናል።

## VCE ማለት ምንድ'ነው?

ተማሪዎችና አስተማሪዎች ስለ VCE ሲናገሩ የቪክቶሪያ ትምህርት የምስክር ወረቀት ማለታቸው ነው። ተማሪዎች የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤታቸውን በሚጨርሱበት ዓመት በጥሩ ውጤት ለማጠናቀቃቸው VCE ያረጋግጣል።

ብዙ ጊዜ የVCE ትምህርት ወደ ሁለት ዓመት ይወስዳል ነገር ግን ረዘም ያለ ግዜም ሊወስድ ይችላል። አንዳንድ የESL ተማሪዎች የVCE ትምህርታቸውን ለሶስት ዓመት የሚሆን ስለሚያራዝሙ የእንግሊዝኛ ችሎታቸውን እንዲያሻሽሉ ጊዜ ሊሰጣቸው ይችላል። ተማሪዎች ማራዘሙ አስፈላጊ ለመሆኑ በአስተማሪዎች ምክር ይሰጣቸዋል።

## VCE እንዴት ይቀነባበራል?

### ጥናቶች

ብዙ ጊዜ ተማሪዎች በዓመት ውስጥ አምስት ወይም ስድስት የትምህርት ዓይነት በVCE ደረጃ ይወስዳሉ። እዚህ የትምህርት ዓይነቶች ጥናቶች ተብለው ይጠራሉ።

### የመለኪያ ክፍሎች

ብዙዎቹ የVCE ጥናቶች አራት የመመዘኛ ክፍሎች ይኖረዋል። አንድ የመመዘኛ ክፍል በሴሚስተር [ፈረቃ ዓመት] ይወሰዳል። የመለኪያ ክፍል 1 እና 2 ትምህርት በ11ኛና በ12ኛ ክፍል እንደ አንድ ክፍል ተደርጎ ሊወሰድ ይቻላል ። የመለኪያ ክፍል 3 እና 4 ትምህርት በ12ኛ ክፍል እንደ አንድ ክፍል በየተራ መወሰድ አለበት። ሁሉም ተማሪዎች የጥናት መመዘኛ ክፍሎችን እንደ VCE ኮርስ በአንድ ጊዜ ለመውሰድ አይገደዱም ይሁን እንጂ የVCE እድል ከማግኘታቸው በፊት ቢያንስ በ16 የመመዘኛ ክፍሎች ጥናት ውጤት "S" [ማለት አጥጋቢ] ውጤት ማግኘት አለባቸው።

### መወሰድ ያለባቸው ጥናቶችና መመዘኛ ክፍሎች

ተማሪዎች ኮርሶችን ሲወስዱ የሚመርጡት የጥናትና መመዘኛ ክፍሎች ለሚወስዱት የእያንዳንዱን ኮርስ ነጥብ የሚያሟላ መሆን አለበት። ተማሪዎች ማሟላት ያለባቸው ነጥቦች ምን ዓይነት የጥናትና መመዘኛ ክፍሎችን መምረጥ እንዳለባቸው አስተማሪዎች መመሪያ ያቀርቡላቸዋል

ተማሪዎች የሚማሩትን ሲመርጡ በቅድሚያ ከትምህርታቸውና ከሥራቸው ጋር እንዲጣጣም ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል። አንድ ተማሪ ለሥራ የሚጠቀመውን ትምህርት ወይም የስልጠና ኮርስ ከ16 የመለኪያ ክፍሎች ውስጥ ስምንቱን ለመውሰድ ከፈለገ በVCE **የሥራ፣ ትምህርትና ስልጠና (VET)** መመዘኛ ክፍሎች ውስጥ ሊሆን ይችላል።

## VCE VET የሥራ፣ ትምህርትና ስልጠና

በVCE ፕሮግራም ውስጥ ያለ የሥራ፣ ትምህርትና ስልጠና ተማሪዎች የVET ሙያ ትምህርት መውሰድ ይችላሉ። ይህ ቅንጅት **VCE VET** ይባላል።

ት/ቤት፤ የስልጠና ተቋማትና ፋብሪካዎች በአንድነት እንዲሠሩ ሲባል ተማሪዎችን ለመርዳት የVCE VET ፕሮግራም በማዘጋጀት ለሥራና ለበለጠ ስልጠና እንዲዘጋጁ ይረዳል። ብዙ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የVET ኮርሶችን ከ VCE በአንድነት በመስጠት አስፈላጊ የሆነው ነጥብ በጥሩ ሁናቴ እንዲሟላ እነዚህ ኮርሶች በአገር አቀፍ ተቀባይነት እንዲያገኙ ይረዳል። ከ40 በላይ የሚሆኑ የVET ኢንዱስትሪ መስኮች ከVCE ትምህርት ጋር በአንድነት የሚሰጥ ሲሆን ብዙ ጊዜ በአብዛኛዎቹ አቅርቦት ይደረጋል።

የVCE VET መስኪያ ክፍሎች ከ1 እስከ 4 ባለው የVCE አሰራር ውስጥ ይካተታል። የVCE VET ፕሮግራምን በተገቢው ለጨረሱ ተማሪዎች በአገር አቀፍ የስልጠና መዋቅር/National Training Framework ውስጥ ተቀባይነት ያለው ሙያ ሊያገኙ ይችላሉ። እንዲሁም አንድ ተማሪ በመመዘኛ ክፍል ከ3 እስከ 4 ደረጃ ከወሰደ ብዙ ጊዜ ለVCE VET የትምህርት ዓይነቶች ውጤት አስተዋጽኦ ይኖራቸዋል። የዚህ ነጥብ ውጤት በአገር አቀፍ የሶስተኛ ትምህርት መግቢያ ደረጃ /Equivalent National Tertiary Entrance Rank (ENTER) አስተዋጽኦ ያደርጋሉ።

ብዙ ጊዜ የVCE VET ፕሮግራሞች በ2 ወይም 3 ደረጃ የምስክር ወረቀት ይሆናል። ተማሪዎች በVCE ያላቸውን የVET ሙያ በጥሩ ውጤት ከጨረሱ [በ2 ወይም 3 ደረጃ የምስክር ወረቀት] በቀጥታ ወደ ከፍተኛ ትምህርት ደረጃ የTAFE ምስክር ወረቀት 4 ሊላኩ ይችላሉ። እንዲሁም ተማሪዎች በትርፍ ሰዓታቸው በVCE ፕሮግራም የአፕረንትሺብ/ሥራና ትምህርት መውሰድ ይችላሉ።

በበለጠ ማብራሪያ ለማግኘት የVCE አስተባባሪን ማናገር ወይም በአካባቢያችሁ የሚገኘውን ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የሥራ አማካሪ አስተማሪን ማናገር።

## እንግሊዝኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ/ESL

እንግሊዝኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ/ESL ለሆነ ተማሪዎች እንግሊዝኛን/ESL እንደ ዋነኛ ጥናት አድርገው ይወስዱታል ። ከዚህ በታች ለሚገኙ ሁለት ነገሮች ከተሟላ አንድ ተማሪ የESL እንግሊዝኛ ሊወስድ ይችላል፡

- ከጥሪ 1 ቀን በፊት በዓመቱ የመመዘኛ ክፍል 3 እና 4 የወሰዱ ታዳያ በአውስትራሊያ የመኖሪያ ፈቃድ ካገኙ ከ7 ዓመት በላይ ላልሆናቸው።
- በጠቅላላው 7 ዓመት የሚይሞላው ተማሪ በመመዘኛ ክፍል 3 እና 4 የወሰደው በእንግሊዝኛ መማሪያ ቋንቋ ካልሆነ።

ተማሪው በልዩ የሆነ ምክንያት እነዚህን ነገሮች የማያሟላ ከሆነ እድሉ ሊሰጠው ይችላል። ለበለጠ ማብራሪያ ለት/ቤቱ ማናገር። ለበለጠ መረጃ የVCAAን በስልክ 9651 4300 ወይም በዌብ ሳይት http://www.vcaa.vic.edu.au መጎብኘት።

## VCE እንዴት ይገመገማል?

VCEን ለመገምገም ሁለት ክፍሎች አሉት፡ በት/ቤት ውስጥ የሚደረግና ከት/ቤት ውጪ በሚሰጥ ፈተና ይሆናል። በዓመቱ መጨረሻ በፈተና የሚገመገሙ ተማሪዎች በVCE በሚደረገው ጥናት የተለየ ሆኖ ያገኙታል። በዓመቱ ውስጥ የሚያካሂዱት ሥራ ይገመገማል እንዲሁም ተማሪዎች የተለያዩ ሥራዎችንና የውጪ ፈተናዎችን ማሟላት ይኖርባቸዋል። ይህ ማለት ተማሪዎች በትምህርት ዓመታት ሁሉ የማያቋርጥ የሥራ ዝግጅት እንዲኖራቸው ይሆናል።

የመመዘኛ ክፍል 3 እና 4 ጥናት የሚያካሂዱ ተማሪዎች የውጪ ፈተናዎችን ወይም የሥራ ኮርስ ማጠናቀቅ አለባቸው። በውጪ ፈተናዎች የሚካኼደው ሥራ ከ A+ እስከ E ነጥብ ድረስ ይሰጥበታል። ብዙዎቹ ፈተናዎች የሚሰጡት በዓመቱ መጨረሻ ሲሆን አንዳንድ ትምህርቶች በዓመቱ አጋማሽና መጨረሻ ፈተናው ይቀርባል።

## በአገር አቀፍ ለሶስተኛ ደረጃ ማስገቢያ የሚተካ(ENTER) ነጥብ
## (Equivalent National Tertiary Entrance Rating)

የVCE ግምገማ ሲያልቅ ነብስ ወከፍ ተማሪ በመግቢያ ነጥብ/ENTER ውጤት ላይ ሪፖርት ይቀርባል። ከሶስተኛ ደረጃ ተቋማት ቦታ ለማግኘት እነዚህ ነጥቦች በሥራ ላይ ይውላሉ።

ወደ ትምህርት ዓለም ለሚመለሱ ተማሪዎች [አዋቂ ተማሪዎች]
ወደ ትምህርት ዓለም የሚመለሱ ተማሪዎች በተያዘው ዓመት ከጥር 1 ቀን እድሚያቸው ቢያንስ 18 ዓመት ሲሆናቸው የVCE ትምህርታቸውን እንዲያጠናቀቁ ይጠበቅባቸዋል። እንዲሁም ቢያንስ ለአንድ ዓመት የሙሉ ቀን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ያቋረጡ መሆን አለባቸው። ተማሪዎች ቢያንስ የVCE ትምሕርት መውሰድ ይኖርባቸዋል።

የVCE ችሎታን ስታሚላ ቢያንስ ከዚህ የሚከተሉት መሚላት ይኖርባቸዋል፡

- ➢ ሁለት የእንግሊዝኛ ክፍሎች
- ➢ ከእንግሊዝኛ ጥናት ሌላ ሶስት ተከታታይ የሆነ የመመዘኛ ክፍል 3 እና 4 ከዚህም ውስጥ ሁለቱ የVCE እና VET በተከታታይ መሆን አለበት

አንዳንድ አዋቂ ተማሪዎች የወደፊት የትምህርት እድላቸውን እንዲያሻሽሉ ተጨማሪ ክፍሎችን መውሰድ ይኖርባቸዋል።

**ለአዋቂ VCE** ኣብዛኛውን ጊዜ በTAFE ኮሌጅ፣ በሁለተኛ ደረጃ ኮሌጅ ወይም በርቀት ትምህርት አማካኝነት ሊወስዱ ይችላሉ።

### በሌላ አገር የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ጨርሰዋል ወይ?

አንዳንድ ተማሪዎች በሌላ አገር የ12ኛ ክፍል ወይም ከዚያ በላይ የትምህርት ደረጃ ያጠናቀቁ ናቸው። እነዚህ ተማሪዎች በሌላ አገር ተመሳሳይ ጥናት እንዳጠናቀቁ ተቀባይነት እንዲያገኙ በVCAA ማመልከት ይችሉ ይሆናል።

VCE ስትማር ክሬዲት/ነጥብ ሊያዝልህና ተመሳሳይ የሆነ ማስረጃ **በተማሪዎች መመዝገቢያና ውጤት ክፍል (Students Records and Results Unit)** ለማግኘት በበለጠ ምክር በስልክ [03] 9651 4402 ለVCAA ማናገር ይቻላል። ተማሪዎች ተመሳሳይ የማስረጃ ጽሁፍ ለማግኘት መቻላቸውን ካሙኑበት ለት/ቤታቸው እንዲያነጋግሩላቸው መጠየቅ ይችላሉ።

## ከVCE ትምህርትህ ጋር የዩኒቨርሲቲ ትምህርት ዓይነት መውሰድ

ጥቂት የተመረጡ ተማሪዎች በአንደኛ ዓመት የዩኒቨርሲቲ ትምህርት ላይ ተጨማሪ የጥናት ፕሮግራም በVCE ትምህርታቸውን መከታተል ይችላሉ። በ VCE **ተጨማሪ** ጥናት በመውሰድ ለአንደኛ ዓመት ዩኒቨርሲቲ የትምህርት ደረጃ ማሻሻል ሲቻል እንዲሁም በሰባት ዩኒቨርሲቲዎች የተለያዩ የትምህርት ዓይነቶች ይቀርባል። እነዚህ የዩኒቨርሲቲ የትምህርቲ ዓይነቶች ከሙሉ ቀን የVCE ፕሮግራም ግዜ የሚወስድና በቁጥር አነስተኛ የሆኑ ጎበዝ ተማሪዎች ብቻ ለዚህ ተጨማሪ ትምህርት ድጋፍ ያገኛሉ።

በበለጠ ማስረጃ እንዴት እንደሚገኝ?
በየዓመቱ VCAA **ለVCE መመሪያ** የሚሆን ጽሁፍ በዌብ ሳይት ለ10ኛ ክፍል ተማሪዎች http://www.vcaa.vic.edu.au/guide02/index.htm ያቀርባል። ስለ VCE **ለሚቀጥለው ዓመት የሚኖሩ ለውጦች ብዙ ጊዜ መረጃ በዚህ መመሪያ ላይ የሚካተት ይሆናል። ለበለጠ ማብራሪያ የመረጃ ኃላፊን በስልክ** 9651 4544 **ወይም** 9651 4328 [**ሜልበርን ላይ ሆኖ የሚደወል**] **ወይም** 1800 134 197 [**በገጠር ሆኖ የሚደወል**] **ማናገር።**

ከዚህ በላይ ያለው መረጃ በ ESL ዌብ ሳይት የትምህርና ስልጠና መምሪያ የተዘጋጀና በ http://www.sofweb.vic.edu.au/lem/esl/index.htm **ላይ ይገኛል። ለዝርዝር መረጃ** በ14 **ቋንቋዎች የተተረጎመ** የ VCE **ዌብ ሳይት ማየት ይቻላል።**

# በቪክቶሪያ የተግባራዊ ትምህርት የምስክር ወረቀት

Victorian Certificate of Applied Learning (VCAL)

[በቪክቶሪያ ስርዓተ ትምህርትና በግምገማ ባለሥልጣን ፈቃድ የወጣ ጽሁፍ፣ ቪክቶሪያ]

## VCAL ምን ማለት ነው?

በቪክቶሪያ ምስክር ወረቀት ተግባራዊ ትምህርት(VCAL) ማለት አዲስ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የምስክር ወረቀት ሲሆን ከተግባር ጋር በተያያዘ ትምህርት የተቀረፕ ነው። 'ተግባራዊ ጥናት' ማለት ተማሪዎች ለበለጠ ትምህርት፣ ስልጠና ወይም ለሥራ እንዲዘጋጁ ችሎታቸውን የሚያዳብሩበት ተጨባጭ የሆነ ኮርስ ነው።

በቪክቶሪያ የምስክር ወረቀት ተግባራዊ ትምህርት(VCAL) ለማግኘት ሶስት ደረጃዎች ይኖረዋል - **መሰረታዊ፣ ማእከላዊና የበላይ ችሎታዎች** ናቸው። የበላይ ችሎታ ከሁሉም በላይ የሆነ ደረጃ ይሆናል። የተማሪዎች ፍላጎትና ችሎታዎች ሲሟላ ደረጃ ማግኘት ይጀምራሉ። ለምሳሌ አንድ ተማሪ ከማእከላዊ ደረጃ ጀምሮ በጥሩ ሁናቴ ከጨረሰ በ12ኛ ክፍል ወደ የበላይ ችሎታ ደረጃ ማለፍ ይችላል። አብዛኛው የአንደኛ ደረጃ ችሎታ ለማጠናቀቅ የዓመታት ፕሮግራም ሊወስድ ይችላል።

## VCAL ማን ነው ሊወስድ የሚችለው?

በ11ኛና 12ኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች መውሰድ ሲችሉ ለልምድ የሚሆን ኮርስ በመውሰድ ፍላጎታቸው እንዲሟላ የVCAL ተዘጋጅተወል። እንዲሁም ሌሎች ተማሪዎች ለምሳሌ በTAFE ተቋማት ለሚማሩ ተማሪዎች ይሆናል።

## ለመግባት የሚያስፈልጉ ነገሮች

ለመግባት የሚያስፈልግ መመዘኛ አይኖሩም። ተማሪዎች ባመቻቸው የትምህርት ደረጃ በVCAL ገብተው መማር ይችላሉ። ለአንድ ተማሪ የትኛው የትምህርት ደረጃ በበለጠ እንደሚስማማው ለመወሰን አስተማሪዎችና የሥራ አማካሪዎች እርዳታ ያቀርባሉ።

## VCAL ለመወሰን ምን ያህል ጊዜ ይወስዳል?

ተማሪዎች በሙሉ ቀን የትምህርት ፕሮግራም በጥሩ ውጤት ከጨረሱ በVCAL የምስክር ወረቀት ያገኛሉ። ለምሳሌ VCAL የማእከላዊ ደረጃ ትምህርት ከ11ኛ ክፍል በማጠናቀቅ በ12ኛ ክፍል የVCAL ከፍተኛ ደረጃ መቀጠል ይሆናል።

## VCAL የት ቦታ ነው የሚወሰድ?

በቪክቶሪያ ውስጥ ብዙ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶችና የTAFE ተቋማት የ VCAL ያቀርባሉ። ተማሪዎች በአካባቢያቸው የሚገኙትን ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶችና የTAFE ተቋማት የ VCAL ትምህርት የሚሰጡ ከሆነ መጠየቅ ይቻላል። ተማሪዎች በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶችና የTAFE ተቋማት መመዝገብ ይገባል ነገር ግን የትርፍ ሰዓት በ VCAL ትምህርት **የአዋቂ ማሕበረሰብ ትምህርት/ Adult Community Education** ድርጅቶችና ሌሎች በማሕበረሰብ የተመሠረቱ የሥራ ቀጣሪዎች ድርጅት በኩል የሚካሔድ ትምህርት መከታተል ይችላሉ።

## በVCAL በኩል ምን ዓይነት ትምህርት ይወሰዳል?
የVCAL የሚያካሂዱ ተማሪዎች ከአስተማሪዎቻቸው/ተንከባካቢ አማካሪያቸው ጋር በመሆን የሚወስዱትን የVCAL መመዘኛ ክፍል ጥናቶች በመምረጥ የመማር ፕሮግራም እንዲዳብር ያደርጋል።

### ክፍል 1- የማንበብ የመጻፍና የቁጥር ትምህርት
VCAL የትምህርት ፕሮግራም የማንበብ፣ መጻፍና የቁጥር ትምህርትን ያጠቃለለ መሆን አለበት። ለምሳሌ ከአጠቃላይ ትምህርት ወደ አዋቂ የምስክር ወረቀት የማንበብ፣ መጻፍና የቁጥር ትምህርት መመዘኛ ክፍሎች ወይም የVCE ሂሳብና እንግሊዝኛ ክፍሎች እንዲሁም እንግሊዝኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ/ **English as a Second Language** (ESL) ክፍሎች ያተቃለለ ይሆናል።

### ክፍል 2- ልዩ ለኢንዱስትሪ የሚሆን ችሎታ
VCAL የትምህርት ፕሮግራም በተለይ ለኢንዱስትሪ የሚሆን ክፍሎችን ከቪክቶሪያ ትምህርትና ስልጠና (VET) ፕሮግራም ወይም VCE VET ያተቃለለ መሆን አለበት።

### ክፍል 3- ለሥራ የሚጠቅሙ ችሎታዎች
VCAL የትምህርት ፕሮግራም በትርፍ ሰዓት ሥራ፣ አዲስ ኣፕረንተሺብስ፣ የሥራ ልምድና ሥራን መሸፈን እንዲሁም ወደ ሥራ ስትዘጋጅ እንደ ጤና አጠባበቅና ደህንነት በተመለከተ ወይም ሥራ ለመጀመር የሚደረግ ቃለ መጠይቅ በትምህርት ክፍሎች ውስጥ የተካተተ ይሆናል።

### ክፍል 4- ነብስ ወከፍ ችሎታን ማዳበር
VCAL የትምህርት ፕሮግራም በአካባቢና በማሕበረሰብ ለተመሰረቱ ፕሮጀክቶች፣ የማይከፈልበት ሥራና በራስ ለመተማመን መንቀሳቀስ፣ በቡድን ሆኖ መሥራትና ሌሎች ለሕይወትና ሥራ የሚጠቅም ችሎታን ማግኘት ያተቃለለ ይሆናል።

## VCAL እንዴት ይገመገማል?
ተማሪዎች በVCAL የሚያካሂዱት ፕሮግራም ለእያንዳንዱ የትምህርት ክፍል አጥጋቢ ውጤት ማግኘት ይኖርባቸዋል። ተማሪዎች የከፍል ውጤት ደረጃ አያስፈልጋቸውም። ተማሪዎች በከፍተኛ ደረጃ ከጨረሱ በVCE መመዘኛ ክፍል 3 እና 4 ተመዝግበው መማር ይችላሉ እንዲሁም ለዚህ የትምህርት ዓይነቶች የሚሆን የከፍል ውጤት ደረጃና ነጥብ ለማግኘት ምርጫ ማካኼድ ይሆናል።

ተማሪዎች ለVCE ወይም VCE VET መመዘኛ ክፍል የሚያስፈልግ ነገር ሲያሟሉ የውጤት መግለጫ ወረቀት ይሰጣቸዋል። ተማሪዎች የVET ወይም ሌላ የትምህርት መመዘኛ ክፍሎችን ሲያሟሉ የምስክር ወረቀት ይሰጣቸዋል ። እነዚህ ጽሁፎች በVCAL ፕሮግራም ጥሩ ውጤት የሚያገኙበትን ዝርዝር ሁኔታ ይገለጻል።

### VCAL በመውሰድ መን ዓይነት ነጥብ ይሰጠዋል?
ተማሪዎች የVET ምስክር ወረቀት ከጀመሩ የሚወስዱት ትምህርት/ጥናት እንደ VCAL ነጥብ ሊቆጠር ይችላል። ተማሪዎች የVCAL ትምህርት ፕሮግራም ለማቀድ ምን ያህል የምስክር ወረቀት እንደተሠራ ማወቅ የአስተማሪዎችና የአማካሪዎች እርዳታ ያስፈልጋል።

ተማሪዎች በVCE የትምህርት ዓይነት ከወሰዱ እንደ VCAL ነጥብ ሊቆጠር ይችላል። አንድ ተማሪ በVCE መመዘኛ ክፍሎች 'S' [አጥጋቢ] ውጤት ማምጣት አለበት።

## ወደ VCE መመለስ

አንድ ተማሪ ሐሳቡን ከቀየረ ወደ VCE መመለስ ይችላል። ማነኛውም የ VCE መመዘኛ ከፍል በጥሩ ሁኔታ ካለቀ እንደ VCAL ነጥብ በመቆጠር ለ VCE ነጥብ ሊያዝ ይችላል። እንዲሁም ወደ VCE የውጤት መዝገብ ሊተላለፉ ይችላል። ሌሎች እንደ VCAL መመዘኛ ከፍል ሲያልቀ እንዲሁም ለ VCE እንደ ነጥብሊያዝ ይችላል- ከአስተማሪ ወይም የሥራ አማካሪ ጋር መወያየት አስፈላጊ ነው።

## በትርፍ ሰዓት መሥራት ይቻላል እንዲሁም/ወይም እየሰሩ በVCAL ትምህርት ለመውሰድ መመዝገብ ይቻላል'ወይ?

ተማሪዎች በVCAL ትምህርት ተመዝገበው እያሉ በትርፍ ሰዓት ሲሠሩ ተቀባይነት ያለው ነጥብ ሊያገኙ ይችላሉ።

- የትርፍ ሰዓት ኣፕረንቲሽፕ ወይም ትሬኒሽፕ
- የትርፍ ሰዓት ሥራ
- በሥራ ምደባ ተከተ መሥራት
- የሥራ ልምድ

## VCAL ካጠናቀቁ በኃላ ምን ሊያገኙ ይችላሉ?

አንድ ተማሪ በትምህርት መሸጋገሪያ፣ ማእከላዊ ወይም ከፍተኛ ደረጃ በጥሩ ውጤት ሲጨርሱ በመሸጋገሪያ፣ ማእከላዊ ወይም ከፍተኛ የVCAL ትምህርት የምስከር ወረቀት ያገኛል። እንዲሁም ተማሪዎች ዝርዝር የVCE VCE VET እንዲሁም የ VCAL መመዘኛ ከፍሎችን የሚገልጽ የጽሁፍ ውጤት እንዲሁም ከ VET ወይም በበለጠ ኮርስ የተሳተፋበትን የጽሁፍ ማስረጃ ያገኛሉ።

አንድ ተማሪ ወደ ዩኒቨርሲቲ ለመግባት ከፈለገ የመግቢያ ነጥብ/ ENTER በVCE ትምህርት ነጥቦች ላይ ሊታሰብ ይችላል። ተማሪዎች ወደ TAFE የምስከር ወረቀት ኮርሶች፣ ወደ ኣፕረንትሺፕስና ትሬኒሽፕ እንዲሁም ሌሎች አዲስ ትምህርትና ስልጠና ለመግባት እንዲቻል በVCAL ትምህርት ይዘጋጃል።

አንድ ተማሪ የVCAL ትምህርት ሲጨርስ እና አዲስ ትምህርት ለማግኘት ከት/ቤት ምክር መጠየቅ ይገባል።

## VCAL ከጨረሱ በኃላይ ወደት መሄድ ይፈልጋሉ?

አንድ ተማሪ የVCAL ትምህርት በመውሰድ በሥራ ዓለም ያለውን ጠቃሚ የሆነ ለምድና ሙያ በማግኘት የተማሪው ወደ ሥራ፣ እየሠሩ መማርና ለበለጠ ትምህርት ወይም እንደ VET ስልጠና ለመቀጠል እንዲችል ይረዳዋል።

አንድ ተማሪ የማንበብ፣ የመጻፍና የቁጥር ትምህርት፣ ከሥራ ጋር የተያያዘ ችሎታ በተለይ ለኢንዱስትሪ ሙያ እንዲያዳብር የVCAL ይረዳል እንዲሁም ለራስና ለሥራ የሚሆን ችሎታና እውቀት ለማግኘት ይረዳል።

በበለጠ ማብራሪያ እንዴት ማግኘት እንደሚቻል?
በአካባቢ ባለ ት/ቤት ወይም TAFE ተቋም ማናገርወይም በቪክቶሪያ ሙያ ባለሥልጣን/Victorian Qualifications Authority ዌብ ሳይት፣ www.vqa.vic.gov.au ምጉብኖይ።

# AMEP የእንግሊዝኛ ቋንቋ ክፍለ ትምህርት

## AMEP English Language Classes

እድሚያቸው ከ 18 ዓመት በላይ ወይም በ16 እና 18 ዓመት መካከል ያሉና የቋንቋ ት/ቤት ላልመረጡ አዲስ ለመጡ ወጣቶች በቅድሚያ በአዋቂ ማይግራንት እንግሊዝኛ ፕሮግራም/**Adult Migrant English Program** (**AMEP**) በሚገኝ የእንግሊዝኛ ትምህርት ክፍሎች ማመልከት አለባቸው።

አዲስ የመጡ ማይግራንት እና የእንግሊዝኛ ቋንቋ ክፍሎች ካስፈለጋቸው የ510 ሰዓታት የእንግሊዝኛ ትምህርት እንዲከታተሉ ይፈቀድላቸዋል ወይም እስከ ለሥራ የሚሆን የእንግሊዝኛ ችሎታ እስኪያገኙ ድረስ ይቀርብላቸዋል። በአካባቢ የሚገኝ የአዋቂ ማይግራንት እንግሊዝኛ ፕሮግራም/AMEP ማእከል በኩል ያላቸውን ተገቢ የሆነ የትምህርት ክፍል ደረጃ በተመለከተ ምክር ያቀርባል። ለእነዚህ ክፍለ ትምህርት በኢሚግሬሽን ጉዳይ መምሪያ Department of Immigration and Multicultural and Indigenous Affairs (DIMIA) በኩል የገንዘብ እርዳታ ይደረጋል።

### በ AMEP ማን ነው የሚማረው?

ከዚህ በታች የተመለከቱትን ነጥቦች የሚያሟላ ሰው በAMEP ፕሮግራም ሊሳተፍ ይችላል፧

- ድሚያቸው 18 ዓመት ወይም በላይ የሆኑ
- በ16 እና 18 ዓመት መካከል ላሉ እና በት/ቤት ባለ የእንግሊዝኛ ክፍሎች መከታተል ለማይችሉ
- ማይግራንት የሆኑና ወደ አውስትራሊያ ከሐምሌ 1 ቀን 1991 በኃላ ለገቡ ወይም
- የመኖሪያ ፈቃድ እስከ ሐምሌ 1 ቀን 1991 ያገኙ [ካልሆነም ማይግራንት ወይም ቋሚ የመኖሪያ ፈቃድ-ጊዚያዊ ቪዛ ላላቸው]
- የ510 ሰዓት ላልወሰዱ
- ለሥራ የሚያገለግል የእንግሊዝኛ ችሎታ ለሌላቸው

### AMEP ለመማር የሚያስችሉ መንገዶች፡

- ቀን፧ ማታ ወይም ቅዳሜና እሁድ
- ሙሉ ቀን ወይም በትርፍ ሰዓት
- በጀማሪ፧ ማእከላዊ ደረጃ ክፍሎች ወይም
- በወጣት የመማሪያ ክፍሎች።

### የAMEP ተሳታፊዎች ማግኘት የሚችሉት፡

- በክፍል ውስጥ ሲማሩ የነጻ ሕፃናት እንክብካቤ
- የኮምፒተር ስልጠና
- የሥራ አማካሪ በነጻ
- የሥራ ልምድ
- ለአዲስ ሰፋሪ ምክር
- የመዝናኛ እንቅስቃሴና ሽርሽር ለወጣቶች።

**በበለጠ ወደ እንግሊዝኛ ክፍሎች የማስገቢያ መንገዶች**
በ AMEP የ460 ሰዓታት ትምህርት ከወሰዱ በኃላ ወይም ለሥራ የሚያገለግል የእንግሊዝኛ ቋንቋ ስታገኝ በAMES ወይም በTAFE ኮሌጆች የተሻለ እንግሊዝኛ ትምህርት መሳተፍ ይቻላል። ለአንዳንድ የእንግሊዝኛ ክፍሎች በሴንተርሊንክ በኩል መመዝገብ ያስፈልጋል።

ለበለጠ ማብራሪያ እንዴት ማግኘት እንደሚቻል?
በ Ascot Vale, Ballarat, Benalla, Bendigo, Box Hill, Broadmeadows, Bundoora, Chadstone, Cobram, Coburg, Collingwood, Dandenong, City/Flagstaff, Footscray, Frankston, Geelong, Hawthorn, Hoppers Crossing, Kyabram, Lalor, Maryborough, Mildura, Mt Waverley, Newborough, Noble Park, Oakleigh, Preston, St Albans, Sale, Shepparton, Springvale, Wangaratta, Warragul, Werribee እና Wodonga **ውስጥ የAMES ትምህርት ማእከላት አላቸው።**
ስልክ፡ 9926 4717 **ወይም በዌብ ሳይት**: www.ames.net.au መጎብኘት።

**የTAFE ኮሌጆች** መረጃ በ TAFE ኮርስ መስመር 131823 **ወይም በዌብ** ሳይት: www.ette.vic.edu.au ይገኛል።

## ቋንቋ፤ የማንበብ፤ መጻፍና የቁጥር ፕሮግራም

Language, Literacy and Numeracy Programme (LLNP)

በኮመንዌልዝመምሪያ የትምህርት፣ ሳይንስ ስልጠና አቅራቢ በቋንቋ፣ የመጻፍ፣ ማንበብና የቁጥር ትምህርት ፕሮግራም **(LLNP)** ወደ ኣውስትራሊያ ለመጡ ወጣቶች እና በ AMEP ስልጠና ጨርሰው ተጨማሪ እርዳታ ለሚያስፈል ጋቸው ሰዎች በነጻ የቋንቋ ስልጠና ይቀርብላቸዋል።

ይህ ስልጠና በቁጥር አነስተኛ በሆነ ቡድን በሳምንት ከ16 እስከ 20 ሰዓታት እንደ ተማሪው ፍላጎት የሚወሰን ለአንድ ዓመት ይሰጣል።

የLLNP ፕሮግራም መሳተፍ የሚችለው በሴንተርሊንክ ተገምግሞ በሴንተርሊንክ በኩል እንደ ሥራ ፈላጊ ሆኖ የተመዘገበ መሆን አለበት።

መሰረታዊ የሆነ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ስልጠና ከዚሕ እንደሚከተለው ይቀርባል፡

- እድሚያቸው ከ15 እስከ 20 ዓመት ላሉ ሥራ ፈላጊዎች የገንዘብ እርዳታ ማግኘት ወይ ማግኘት ለማይችሉ
- እድሚያቸው ከ20 ዓመት በላይ ለሆኑ እና ለወጣቶች የሚሰጥ አበል፣ ለሥራ መፈለጊያ አበል ወይም ለወላጅ የሚሰጥ አበል ለሚከፈላቸው ይሆናል።

ከዚህ በላይ ያሉትን አበሎች የማያገኙ ሥራ ፈላጊዎች እና የጊዚያዊ ወይም የመቆያ ቪዛ Subclasses 309, 310, 445,450, 820, 826, 850, 437, 781, 783 እንዲሁም 784 ያላቸው ሰዎች መሰረታዊ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ስልጠና ማግኘት ይችሉ ይሆናል። በሶሻል ሰኩሪቲ የሁለት ዓመት ቆይታ የጊዜ ገደብ የተወሰነባቸው ማይግሬንትስይህ ጉዳይ ይመለከታቸዋል።

ከፍተኛ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ስልጠና የሚቀርበው፡
- ዜግነት፣ ቋሚ ነዋሪ ለሆነ ወይም የጊዚያዊ መቆያ ቪዛ Subclasses 309, 310, 445,450, 820, 826, 850, 437,781, 783 እንዲሁም 784 ላላቸው ሥራ ፈላጊዎች። የስልጠና እድል ለማግኘት የገቢ ምንጭ ምጣኔ እርዳታ አስፈላጊ አይደለም።

ስልጠና የሚያቀርቡ አካላት በሴንተርሊንክ ውስጥ ስለሚገኙ ቅርበት ባለው አመልካቾች አገልግሎት ማግኘት ሲችሉ ሴንተርሊንክ ቀጠሮ በማዘጋጀት ውሳኔ ይሰጣል። ሙያ ላላቸው ሰዎች በመሠረታዊ ወይንም በከፍተኛ የእንግሊዝኛ ስልጠና መመደብ እንዳለባቸው ገምጋሚው ውሳኔ ይሰጣል።

ስልጠና የሚያቀርቡ አካላት ከTAFE ኮሌጆች እስከ ማሕበረሰብ አቅራቢዎች ይለያያል እንዲሁም ፈቃድ ያላቸውን የግል ማሰልጠኛ ድርጅቶች ያካተተ ይሆናል።

በገጠር ለሚኖሩ ተማሪዎች ወይም የትምህርት ክፍሎችን ማግኘት ለማይችሉ በርቀት የትምህርት ፕሮግራም አማካኝነት ማግኘት ይችላሉ። ይህም በሴንተርሊንክ በኩል ሊቀናጅ ይችላል።

ለበለጠ ማብራሪያና ወደ ፕሮግራም እንድትላክ የአካባቢን ሴንተርሊንክ መጎብኘት ነው። እንዲሁም ስለ ፕሮግራሙ በኢንተርኔት http://www.llnp.dest.gov.au መጎብኘት ይሆናል።

# የሙያና ተጨማሪ ትምህርት
## Technical and Further Education (TAFE)

TAFE የትምህርት ተቋም ሲሆን ሰፋ ያለና የተለያዩ የሙያና ትምህርታዊ ደረጃዎች ያቀፈ ስልጠና የሚሰጥበት አካል ይሆናል። አብዛኛው ስልጠና በTAFE ተቋማት አማካኝነት ይቀርባል። የአዋቂ ማሕበረሰብ ትምህርት አሰጣጥ እንዲሁም በግል የሚያቀርቡም ቢሆን ፕሮግራም ያዘጋጃሉ።

ትምህርት የሚሰጥባቸው መስኮች፡
- የእርሻ፣ እንስሳ ትምህረትና የተፈጥሮ ሃብት
- የሕንጻና ፕላን ንድፍ
- የስነ-ጥበብ፣ የእጅ ሥራ ሙያ፣ ሙዚቃ፣ እስከታ
- የንግድ፣ ኢኮኖሚ፣ አያያዝና የሽያጭ
- የኮምፑተርና ኢንፎርሜሽን አሠራር
- የትምህርት
- የኢንጂነሪንግና ተመሳሳይ ቴክኖሎጂዎችና ጥናቶች
- የጤና ጥበቃ፣ ማሕበረሰብና የምቾት አገልግሎት
- የእንግዳ መቀበል፣ ቱሪዝም፣ ትራንስፖርትና ነብስ ወከፍ አገልግሎት
- የሰብዓዊና ማሕበራዊ ሳይንስ
- የሕግና ደሕንነት
- የምርት ሥራ ውጤቶች አጠቃቀም
- የሳይንስ

ወደ TAFE ኮርሶች የመግቢያ ትምህርትና የችሎታ ደረጃ የተለያየ ይሆናል። ከዚህ በታች እንደተጠቀሰው ሊለያይ ይችላል፡
- ቀደም ብሎ ት/ቤት ላቋረጡ [የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ላልጨረሱ]
- የVCE ትምህርት ላጠናቀቁ /የአስራ ሁለተኛ ትምህርት ለጨረሱ
- ችሎታ ያላቸው ባለሙያዎች/ቀደም ሲል የሥራ ልምድ ያላቸው ወይም
- ከትምህርታቸው የተጓጉሉ አዲስ የመጡ ወጣቶች

### ሙያዎች

የTAFE ኮርሶች ላጠናቀቁ የምስክር ወረቀት ይሰጣል። የTAFE ሙያ በአገር አቀፍ ስልጠናና አሠራር **(National Training Framework)** የታወቀና በአገር አቀፍ ተቀባይነት ያገኘ ይሆናል። ይህ ማለት የTAFE ሙያ በሞላው አውስትራሊያ ተቀባይነት አለው ማለት ነው።

በTAFE ውስጥ የሚገኙ ሙያዎች፡
- ምስክር ወረቀት I
- ምስክር ወረቀት II
- ምስክር ወረቀት III
- ምስክር ወረቀት IV
- ዲፕሎማ
- ከዲፕሎማ በላይ
- የመጀመሪያ ዲግሪ

እንዲሁም TAFE በተለይ አስፈላጊ በሆኑ የዲግሪ ኮርሶች ማዘጋጀት ይችላል።

ብዙ ጊዜ የTAFE ኮርሶች በሙሉ ቀን ወይም በአመቺ ጊዜ መውሰድ ይቻላል። የምስክር ወረቀት ከ1 እስከ 3 ላሉ ኮርሶች አብዛኛው በሙሉ ቀን ሲወሰድ ከ12 ወር ጊዜ በላይ አይወስድም። የዲፕሎማና ከዲፕሎማ በላይ ላለ ኮርስ በሙሉ ቀን ትምህርት ወደ ሁለት ዓመት ይወስዳል። ለዲግሪ የሚወሰድ ኮርስ የሶስት ዓመት ወይም አራት ዓመት ትምህርት ይፈልጋል።

እንዲሁም በTAFE የአፕረንትሽፕ/ Apprenticeship ወይም የትሬኒሽፕ/Traineeship ስልጠናዎች ይቀርባሉ። በሥራና ትምህርት የApprentiship ወይም የTraineeship ስልጠና ከመመዝገብህ በፊት በ TAFE ስትማር እያለ እየሠራሕ ስልጠና ለማከናወን ውል የሚገባልሕ ቀጣሪ/አሠሪ ኣካል ማግኘት አለብሕ። ብዙ ጊዜ Apprentiship ለመጨረስ አራት ዓመት ሲወስድ የTraineeship ደግሞ አንድ ዓመት ይወስዳል።

## የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት

የTAFE ተቋማት የእንግሊዝኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ/ESL ፕሮግራም ያካሂዳሉ። እነዚህ ፕሮግራሞች ተጨማሪ እንግሊዝኛ ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች ሲሆን በቀድሚያ ትምህርታቸው ወይም ለሥራቸው እንዲያሻሽሉ እድል ሊከፍትላቸው ይችላል። ብዙ ጊዜ ሰዎች የአዋቂ ማይግሬንት ሁለገብ ባህላዊ ትምህርት/AMES ወይም የቋንቋ ማእከል ኮርሶች መጨረስ ይኖርባቸዋል። የጊዚያዊ መኖሪያ ፈቃድ ላላቸው ሰዎች በTAFE /ESL ኮርሶችን ለመውሰድ መመዝገብ ይችላሉ።

አዲስ ለመጡ ስደተኛ ወጣቶች ልዩ የሆነ የ ESL መሸጋገሪያ ፕሮግራሞች ይኖራል። ቀደም ሲል ያላቸው ቋንቋ የማንበብና የመጻፍ ችሎታ ደረጃ ቢኖራቸውም በነዚህ ፕሮግራሞች መግባት ይችላሉ። እንዲሁም የሁለተኛ ደረጃ ትምሕርት ጨርሰው ሶስተኛ ደረጃ ትምህርት ለጀመሩ በዚህ ፕሮግራም መሳተፍ ይችላሉ።

አዲስ ለመጡ ወጣቶች በኖርዝ ሜልበርን የTAFE ተቋም [በፕሪስተንና ኮሊንግውድ የሚሰጥ የ YAMEC ፕሮግራም]፤ በፋትስክሬይ ቪክቶሪያ ዩኒቨርሲቲ (TAFE)፤ በዳንዴኖንግ ቺስሆልም ተቋም የሚቀርብ ፕሮግራም **የተለየ የመሸጋገሪያ እንግሊዝኛ ፕሮግራም/ESL** ይሰጣል። ትምህርታቸውን ለቋረጡ ወጣቶች ሰፋ ያለ ትምህርትና እንግሊዝኛ ለሚፈልጉ እነዚህን ፕሮግራሞች ግምት ላይ ማስገባት ይሆናል። ሒሳብ፤ ሳይንስ፤ ኢንፎርሜሽን/መረጃ ቴክኖሎጂ፤ የመዝናኛ ፕሮግራሞች እንዲሁም ከሰፈራ ጋር በተያያዘ ጉዳዮች ላይ ማለት እንደ መኖሪያ ቤት፤ ሴንተርሊንክ፤ ጤናና ሕጋዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ በዚህ ፕሮግራም ሊቀርቡ ይችላሉ። ተማሪዎች ያላቸውን የእንግሊዝኛ ችሎታ ደረጃ (ASLPR) በፕሮግራሙ ላይ ማስገባት እንደሚቻል ነው።

እያንዳንዱ የTAFE ስደተኛ ወጣቶች ፕሮግራሞች ከሌሎች ጋር በመሆን አገልግሎት ያቀርባሉ፤ ማለት ከJPET, MIPs. JPP ጋር ቅንጅት በመፍጠር ለወጣቶች እርዳታ ማቅረብ ይሆናል። እነዚህ እርዳታ አቅራቢዎች ከTAFE ስደተኛ ወጣቶች ፕሮግራም ሠራተኛ በመተባበር ለሰፈራ በሚያስፈልጉ ጉዳዮች ማለት የቤትና የጤና ጥበቃ ፍላጎትን ለማሟላት አገልግሎቶችን ማቅረብ ይሆናል።

የTAFE /ESL ተማሪዎች ለሥራ የሚጠቅም ትምህርት ከESL ጋር ሊጠቃለል ይችላል፤ ለምሳሌ እንግሊዝኛን ከሪፖርት ጋር ማያያዝ ወይም እንግሊዝኛን ከሕፃናት እንክብካቤ ጋር ማያያዝ ወዘተ. በሌሎች ክፍሎች ያሉ ጥሩ እንግሊዝኛ የሚናገሩ በማንበብና መጻፍ ላይ ትኩረት ሲደረግላቸው ነገር ግን ተጨማሪ የማንበብና መጻፍ እርዳታ እንደሚያስፈልጋቸው ነው። እንግሊዝኛ ክፍሎች በቀንና ምሽት የሚሰጥ ሲሆን የሙሉ ቀን ወይም የትርፍ ሰዓት ከፍለ ትምህርት ሊሆን ይችላል።

ወደ TAFE ተቋማት መግባት
TAFE የሚቀያየር የመግቢያ ፖሊሲ ሊኖረው ሲችል በመደበኛ ትምህርትና በልምድ በተገኘ ችሎታ የሥራ ልምድ ተቀባይነት ይኖረዋል።

ይህ ማለት አንድ ሰው ሌላ ጠቃሚ የሆነ ልምድ ካለው ወደ TAFE ለመግባት ሁልጊዜ የመደበኛ ትምህርት መጨረስ አለብሕ ማለት አይደለም። በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ ይህ አስፈላጊ የሆነ ልምድ በTAFE ኮርሶች ላይ ነጥብ ሊያስገኝ ይችላል። እንዲሁም **በቅድሚያ ትምህርት/Recognition of Prior Learning (RPL)** ተቀባይነት ያለው ይባላል።

ወደ አንዳንድ ኮርሶች ለመግባት በቀጥታ ወደ TAFE ማመልከት ሲሆን ነገር ግን ለሌላ ልዩ የሆነ ዲፕሎማና ከዲፕሎማ በላይ ላለ ደረጃ **በቪክቶሪያ ሶስተኛ ደረጃ ትምህርት መቀበያ ማእከል /Victorian Tertiary Admission Centre (VTAC)** ተደርጎ ማመልከቻ ማስገባት አስፈላጊ ይሆናል። ይህ በሚሆንበት ጊዜ በመስከረም ወር ከዓመት በፊት ይሆናል። ዝግይቶ ለሚያመለክት ሰው የገንዘብ ቅጣት ይኖረዋል። የTAFE ኮርሶች በጥር ወር እንዲሁም በሐምሌ ወር [የአጋማሽ ዓመት] ይጀምራል።

ለበለጠ ዝርዝር ሁኔታ የTAFE ተቋማትን መጠየቅ ነው።

## ዩኒቨርሲቲ ለመግባት የTAFE አስፈላጊነት

የTAFE ምስክር ወረቀት ወደ ሌላ ትምህርት በዩኒቨርሲቲ ለመቀጠል የሚረዱ ኮርሶችን ያጠቃለለ ይሆናል። አንድ ተማሪ የዲፕሎማ ወይም ከድፕሎማ በላይ ኮርሶችን ከጨረሰ በዩኒቨርሲቲ ውስጥ የዲግሪ እድል ለማግኘት አንዳንድ ነጥቦችን ሊያገኝበት ይችላል። በዩኒቨርሲቲ ዲግሪ ለመውሰድ ሶስት ዓመት የሚጨርስ ከሆነ የሚገኘው ነጥብ የአንደኛ ዓመትን ትምህርት የሚመጣጠን ሊሆን ይችላል።

## ለትምህርት ክፍሎች የሚከፈል ገንዘብ

በTAFE ለመመዝገብ ክፍያ ሲኖረው እንዲሁም ለተማሪዎች አገልግሎት ለሚውሉ ነገሮች ሊከፈል ይችላል። የTAFE ክፍያ ዋጋ ከዩኒቨርሲቲ HEC ክፍያ ጋር ሲነጻጸር በጣም አነስተኛ ይሆናል።

ለወጣቶች የሚከፈል አበል የሚያገኝ ተማሪ ወይም የሴንተርሊንክ ኣበልና የቅናሽ ዋጋ ለመክፈል ይችላሉ። አብዛኛው ኮርሶችን የሚወስዱ ተማሪዎች ለወጣት የሚሰተ አበል ማግኘት እንደሚችሉ ነው። ለበለጠ ዝርዝር ሁኔታ "የገቢ ምንጭ እርዳታ" /“Income Support” የሚለውን ማንበብ ይሆናል።

ተማሪዎች ለመመዝገቢያ የሚሆን የገንዘብ እርዳታ ከፈለጉ ብድር ማግኘት ይችሉ ይሆናል።

### የበለጠ መረጃ እንዴት ማግኘት እንደሚቻል?

TAFE ተቋማት በሞላው ሜልበርን ይገኛሉ። እያንዳንዱ ተቋም ማብራሪያ በማቅረብ ለመርዳት ኃላፊ አለበት። እንዲሁም ትምህርት ለመቀጠል የሚፈልጉ የሥራ አማካሪ አገልግሎት ይሰጣቸዋል።

ስለ TAFE በበለጠ ማብራሪያና በፕሮግራሙ ስሚቀርበው መረጃ ለማግኘት፡

- "ስለ TAFE ጥያቄና መልስ" የሚል በነፃ የሚቀርብ ትንሽ መጽሐፍ [በት/ ቤትና በሕዝብ ቤተ መጻሕፍት ውስጥ ይገኛል]
- በቪክቶሪያ ምክር ሰጪ፡ ስልክ፡ 1300 366 356
- በሶስተኛ ደረጃ ትምህርት ስልጠና ጽ/ቤት ዌብ ሳይት፡ www.otte.vic.gov.au

# የኒቨርሲቲዎች

በዩኒቨርሲቲ ውስጥ የተለያዩ ኮርሶች ሲቀርቡ አንዳንዱ ኮርስ ወደ ሥራ የሚመራ ማለት እንደ ሕክምና፣ ነርስ ወይም ኢንጂነሪንግ እንዲሁም በበለጠ አጠቃላይ በሆነ እንደ ኪነ ጥበብ ወይም ሳይንስ የመሳሰሉ ናቸው።

የሚሰጡ የኮርስ ዓይነቶችም፡

- **ዲፕሎማ፡**
  ሁለት ዓመት የሙሉ ቀን ወይም ተመሳሳይ የትርፍ ሰዓት ትምህርት ይሆናል። የሚያካሂዱት ሙያ ተግባራዊ ችሎታና አጠቃላይ ግንዛቤ በማግኘት እንደ ማንኛውም ባለሙያ እውቀት እንዲኖራቸው ያተኮረ ነው።
- **ከዲፕሎማ በላይ፡**
  ሶስት ዓመት የሙሉ ቀን ወይም ተመሳሳይ የትርፍ ሰዓት ትምህርት ይሆናል። በዚህ ጥናት ከዲፕሎማ የበለጠ ደረጃ የያዘ ሲሆን ነገር ግን አንዳንድ ተግባራዊ የሆኑ ችሎታዎች ይፈለጋሉ።
- **የመጀመሪያ ዲግሪ፡**
  ከሶስት እስከ አራት ዓመት የሙሉ ቀን ወይም ተመሳሳይ የትርፍ ሰዓት ትምህርት ይሆናል። ብዙ ጊዜ አንድ ተማሪ ከብዙ ኮርሶች ውስጥ በአነስተኛ አንድ ለየት ያለ የትምህርት ዓይነት ማጥናት አለበት።
- **በምስክር ወረቀት መመረቅ፡**
  የስድስት ወር የሙሉ ቀን ወይም ተመሳሳይ የትርፍ ሰዓት ትምህርት ይሆናል። ቀደም ሲል በድሕረ ምርቃ ኮርስ የተገኘው እውቀት ወይም የሥራ ትምህርት ችሎታ በአዲስ የሙያ ችሎታ ማስፋፋት ይሆናል።
- **በዲፕሎማ መመረቅ፡**
  አንድ ዓመት የሙሉ ቀን ወይም ተመሳሳይ የትርፍ ሰዓት ትምህርት ይሆናል። ቀደም ሲል ከመመረቅ በፊት በተወሰደ ኮርስ የተገኘው እውቀት ወይም የሥራ ትምህርት ችሎታ በአዲስ የሙያ ችሎታ ማስፋፋት ይሆናል።
- **ማስተር ዲግሪ፡**
  ሁለት ዓመት የሙሉ ቀን ወይም ተመሳሳይ የትርፍ ሰዓት ትምህርት ይሆናል። ይህ ዲግሪ የሚሰጠው የራሱ የሆነ የምርምራ ፕሮጀክት ያቀፈ ጽሁፍ ቴሲስ ሲቀርብና ይህ ጽሁፍ በሆነ የትምህርት ዓይነት ጥሩ አመለካከትና ግንዛቤ ያለው ችሎታ ሲያሳይ ይሆናል።
- **ዶክትሬት ዲግሪ፡**
  ሶስት ዓመት የሙሉ ቀን ወይም ተመሳሳይ የትርፍ ሰዓት ትምህርት ይሆናል። ይህ ዲግሪ የሚሰጠው ከሥራ ጋር በተያያዘና ለየት ባለ የሙያ ችሎታ ለማሻሻል ይሆናል። አንድ ተማሪ በማንኛውም የችሎታ መመዘኛ ኮርስ ወይም ምርምር በማካሄድ የሚገኝ ጥልቀት ያለው ግንዛቤና እውቀት ይሆናል።

## አነስተኛ የሆነ የመግቢያ ነጥብ

አንድ ተማሪ ወደ ዩኒቨርሲቲ ለመግባት የVCE ትምህርት በጥሩ ውጤት መጨረስ አለበት ወይም በTAFE ትምህርት መቀጠል ይኖርበታል ወይም በልዩ **የመግቢያ ዝግጅት/Special Entry Provisions** ችሎታ ያለው መሆን ይገባል።

## ልዩ የመግቢያ ዝግጅት/Special Entry Provisions

ትምህርት አቋርጠው እንደገና ለሚያመለክቱ ሰዎች ካልሆነ በስተቀር ሌሎች ሲያመለክቱ በሚያመለክቱበት ተቋም የእያንዳንዱን ተማሪ ሁኔታ ግምት ውስት በማስገባት ይሆናል። አመልካቾች በተቋሙ የሚኖራቸው የሥራ ታሪክ፣ የድሕረ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ወይም ልዩ ሁናቴ ግምት ውስት በማስገባት ይሆናል። የመግባት እድል በአንድ ወይም በበለጠ ሁኔታዎች ማለት እንደ በእድሜ፣ ትምህርት መብሰል ወይም በማሕበራዊ ችግር የደረሰበት ወይም የማሸነፍ ችሎታ መሰረት በማድረግ ይሆናል። አመልካቾች በዩኒቨርሲቲ ገብተው ምን ያህል የመከታተል ችሎታ እንደሚኖራቸው በመግቢያ ፈተና ይረጋገጣል።

## የVCE ትምህርት ለጨረሱ ተማሪዎች የሚያስፈልግ ኮርስ

አንድ ተማሪ ለከተኛ የመግቢያ ነጥብ በጥሩ ውጤት ማሟላት ሲገባው እንዲሁም ማመልከት ለሚፈልጉት ለእያንዳንዱ ልዩ የኮርስ ትምህርት ዓይነቶች ነጥብ ማሟላት ይኖርበታል።
ለዚሕ ኮርስ የሚያስፈልጉ ነጥቦች፡

- **ቅድመ ጥናት የሚያስፈልግ፡**
  አንድ ተማሪ ጥናት ከመጀመሩ በፊት ትምህርቱን በጥሩ ሁኔታ ያጠናቀቀ መሆን አለበት።
- **መካከለኛ ውጤት/ነጥብ**
  ከጥናት በፊት ግምት ውስጥ መግባት የሚኖርበት ጉዳይ ቢኖር በአንዳንድ ምክንያት በት/ቤት የሚደረግ የግምገማ መዋቅር/School Assessed Tasks (SATs) ነጥብ መሟላት አለበት።

## በቪክቶሪያ ሶስተኛ ደረጃ ኮርሶች ለመግባት እንዴት ማመልከቻ እንደሚቀርብ

በቪክቶሪያ TAFE ለሚወስዱ ተማሪዎች የሙሉ ቀን የምስክር ወረቀት IV፣ ዲፕሎማና ከዲፕሎማ በላይ አብዛኛው በዩኒቨርሲቲ ውስጥ ለሚወሰድ ዲግሪ ወይም የዲፕሎማ ኮርሶች የሚቀርብ ማመልከቻ **በቪክቶሪያ የሶስተኛ ደረጃ መግቢያ ማእከል** (VTAC) ይወሰናል። የቪክቶሪያ ሶስተኛ ደረጃ መግቢያ ማእከል (VTAC) በሐምሌ ወር ስለ ማመልከቻ የሚገልጽ ትንሽ መጽሐፍ ሲያወጣ በዩኒቨርሲቲና TAFE ኮርሶችን ለመውሰድ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን እንዲሁም የማመልከቻ ቀጾችን እንዴት እንደሚሠራ ምክር አዘል ጽሑፍ ይሆናል። ለድሕረ ምርቃ ኮርሶች **ንለማመልከት** የሚወስደው ጊዜ ምርጫ ከማካኄድህ ከአንድ ዓመት በፊት በመስከረም መጨረሻ ይሆናል።

ለማንኛውም ኮርሲ **አመራርጥ** በውድድር ሲሆን ከጥቂት ለየት ያለ ሁኔታ ካላቸው በስተቀር በትምህርት አካዳሚ ብልጫ ሲሖን ይህም በሥራ የተገኘ ልምድ፣ ልዩ ችሎታ፣ ጠባይ ወይም ለሙያ የሚስማማ ሁኔታን ያጠቃለለ ይሆናል።

# ከፍተኛ የትምህርት አስተዋጽኦ አሰራር

Higher Education Contribution Scheme (HECS)

የቋሚ መኖሪያ ላላቸው ተማሪዎች እና ለሚወስዱት ኮርስ በ**ከፍተኛ የትምህርት አስተዋጽኦ አሠራር (HECS)** በኩል ክፍያ ይካኼዳል። አንድ የሙሉ ቀን ተማሪ ለሚወስደው መደበኛ ትምህርት HECS በየዓመቱ ከ $3500 ዶላር እስከ $6 000 ዶላር ያስከፍላል። ብዙ ጊዜ ክፍያው ሊቀም ወይም የገቢ መጠን ግብር/ታክስ ከተወሰነው ደረጃ እስኪደርስ እንዲሁም የገቢ መንጩ ከመቶ ታስቦ ለአውስትራሊያ ታክሴሽን/ግብር ሰብሳቢ ጽ/ቤት የሚከፈል ተያዥ ሊሆን ይችላል።

አንዳንድ ኮርሶች የ HECS አሠራር የላቸውም ነገር ግን የዓመት ሙሉ ክፍያ $10 000 ዶላር የሚሆን በቅድሚያ ያስከፍላል።

## ለበለጠ ማብራሪያ እንዴት ማግኘት እንደሚቻል?

ለትምህርት፣ ሳይንስና ስልጠና መምሪያ (DEST) ከፍተኛ ትምህርት ዌብ ሳይት:
http://www.dest.gov.au/highered/indexl.htm መጎብኘት ይሆናል።

እንዲሁም አንዳንድ ኮርሶችን ያቀፈ ትንሽ መጽሐፍ ውስጥ በዩኒቨርሲቲው ይሰጣል። ይህ መጽሐፍ ለእያንዳንዱ ዩኒቨርሲቲ በመጠየቅ ማግኘት ይቻላል።

**ስለ ሶስተኛ ደረጃ ትምህርት አመራረጥ እንዲሁም ኣሠራር ለቪክቶሪያ ሶስተኛ ደረጃ ትምህርት አመራር ማእከል** (VTAC) **በቀጥታ በስልክ**: 1300 364 133 **መጠየቅ ወይም በዌብ ሳይታቸው፥** www.vtac.edu.au **ማየት ወይም መጽሐፉ ካስፈለጋቸሁ፡**

The Information Officer
Victorian Tertiary Administrations Centre (VTAC)
Suite B, 40 Park Street
SOUTH MELBOURNE VIC 3205

# ለገቢ ምንጭ እርዳታ

አንድ ወጣት ትምህርቱን እስኪጨርስ በሴንተርሊንክ በኩል የተወሰነ የፋይናንስ/ገንዘብና ሌሎች እርዳታዎችም ይሰጠዋል።

## ለወጣቶች የሚሰጥ አበል/ክፍያ/Youth Allowance

የገንዘብ አበል ማግኘት የሚችል፤

- እድሚያቸው ከ16 እስከ 24 ዓመት ያሉና የሙሉ ቀን ተማሪ ለሆኑ
- እድሚያቸው 25 ዓመት የሆነና የሙሉ ቀን ተማሪ ለሆኑ ወይም እድሚያቸው 25 ዓመት ከመሙላቱ በፊት ለወጣት የሚሰጥ አበል ያገኙ ለነበረ እና እስከ አሁን ድረስ ተመሳሳይ ኮርስ ለሚሳተፉ ተማሪዎች
- እስከ 21 ዓመት እድሜ ላሉ ሌሎች ወጣቶች እና የሙሉ ቀን ሥራ ያላቸው፤ ትምህርትና ሥራን በፈረቃ ለሚያኪሂዱ፤ ሌላ የሥራ ፈቃድ ላላቸው [በፈቃደኘነት ያለ ደመወዝ ለሚሠሩ] ወይም ለታመሙ ወጣቶች
- እድሚያቸው 15 ዓመት ሞልቶ ት/ቤት ለመተው እድሜው ለደረሰ ወጣት እራሱን እንደቻለ ስለሚቆጠር ይሆናል።

እድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች ከሆኑ የ12ኛ ክፍል ትምህርት ያላጠናቀቁ ወይም ተመሳሳይ የሆነ የሙሉ ቀን ትምህርት ወይም ስልጠና የማይከታተሉ ወጣቶች አበል አይሰጣቸውም። ለወጣት የሚሰጥ አበል ለማግኘት ት/ቤት መሄድ፤ በTAFE ወይም ሌላ የታወቀ የስልጠና ኮርስ መሳተፍ ይገባዋል። በነዚህ የመግቢያ ነጥቦች ነጻ መሆን የሚችለው አመችና የማይቻል ከሆነ ነው።

አንድ ወጣት ብቻውን የሚኖር ወይም ከሰው ጋር ተጠግቶ የሚኖር ከሆነ፤ ትዳር ከሌለው፤ ልጆች ከሌሉት፤ በቤቱ የሚኖር ወይም ለትምህርት ሲል ከቤቱ ርቆ የሚኖር ከሆነ ወይም የሥራ እድል ካሸሻለ የሚከፈለው አበል መጠን በዚሁ መሰረት ይወሰናል።

ከሰው ጋር ተጠግቶ የሚኖር ወጣት አበል እንዲከፈለው ወይም የአበሉ መጠን የሚወሰነው የወላጅ ገቢ መጠን፤ የንብረትና የቤተሰብ ሁኔታ መነሻ በማድረግ ይሆናል። የግል ቤት ከራይ ለሚከፍሉ ወጣቶች የቤት ከራይ መደጎሚያ ገንዘብ ሊሰጣቸው ይችላል። በበለጠ ማብራሪያ ለማግኘት ሴንተርሊንክን መጠየቅ ይሆናል።

## ለተማሪዎች የሚከፈል/ Austudy

- ይህ ለተማሪዎች የሚሰጥ ክፍያ/አበል እድሜያቸው 25 ዓመት ወይም በላይ ለሆኑና የሙሉ ቀን ኮርስ ፈቃድ ባለው ተቋም ውስጥ ለሚከታተሉ ይሆናል። ላካለ ስንኩል ለሆኑ ተማሪዎች የተርፍ ሰዓት ትምህርት እንዲያገኙ መርዳት ይቻላል።

### ልዩ አበል/ጥቅም/Special Benefit

የተለየ አበል የሚሰጣቸው የገንዘብ ችግር ላለባቸው ሰዎችና በሴንተርሊንክ ውስጥ ሌላ ዓይነት ክፍያ ማግኘት ለማይችሉ ይሆናል።

### የገቢ መጠንና የንብረት መመዘኛ

ልጆች እራሳቸውን እስኪችሉ ድረስ ከተቻለ ወላጆች እርዳታ እንዲያደርጉ ይገባል። በዚህ ሁኔታ ላሉ የወላጅ የገቢ መጠን ግምት ላይ በማስገባት ወጣቶች አበል ለማግኘት ወይም አለማግኘት ይወሰናል።

- **የወላጅ አማካይ ንብረት መመዘኛ/ Parental Means Test** የሚደረገው ወጣቱ አበል ማግኘት መቻሉን ለማረጋገጥ ብቻ ይሆናል። የወላጆች ንብረት፤ የገቢ መጠንና የቤተሰብ አማካይ የገቢ መጠን ግምት ውስጥ በማስገባት ወላጆች ለልጆቻቸው ምን ያህል መርዳት እንደሚችሉ መመዘኛ ይሆናል።

- **የግለሰብ ገቢ መጠን መመዘኛ/ Personal Income Test -** በየሁለት ሳምንት የሚሰጥ ለወጣተቶችና ተማሪዎች ነብስ ወከፍ ያላቸው የገቢ መጠን ግምት ውስጥ በማስገባት ይሆናል።
- **የግለሰብ ንብረት ገመመዘኛ/ Personal Assets Test -** ለተማሪዎች አበልና እራሳቸውን ላልቻሉ አበል ለሚያመለክቱ ወጣቶች ተግባራዊ ይሆናል።
- **ለባለ ትዳር የገቢና የንብረት መመዘኛ/ Partner Income and Assets Tests -** ለተማሪዎች አበልና እራሳቸውን ላልቻሉ አበል ለሚያመለክቱ እና ከባለትዳር ጋር አብረው ለሚኖሩ ወጣቶች ተግባራዊ ይሆናል።

## ነዋሪነት

አንድ ሰው ክፍያ ለማግኘት ማመልከት የሚችለው በአውስትራሊያ ቋሚ የመኖሪያ ፈቃድና ነዋሪ ከሆነ ነው። አንዳንድ የሙሉ ቀን ተማሪዎች ከአውስትራሊያ ውጪ እያሉ አበል ይከፈላቸዋል። አዲስ የመጣ ማይግራንት ለወጣቶችና ለተማሪዎች የሚከፈል አበል ከማግኘቱ በፊት ለሁለት ዓመታት መቆየት አለባቸው። በሰደተኛና በሰብዓዊ ቪዛ ለመጡ ወጣቶች ከዚህ ገደብ ነጻ ይሆናሉ። አስተርጓሚ ሲያስፈልግ በነጻ ሊቀናጅ እንደሚችል ነው።

## ተጨማሪ ጥቅም

ከዚህ በታች ያለ ጥቅሚ/ክፍያ ሊሰጥ ይችላል፡
**የቤት ኪራይ መደጎሚያ** የሚከፈለው ለሚማር ወይም ሥራ ለሚፈልግ ተከራይ ወጣት ይሆናል።

**ከወለድ ነጻ የሆነ ክፍያና ልዩ ቅድሚያ የሥራ ክፍያ፡** የወጣትና ተማሪ አበል የሚያገኙ ከወለድ ነጻ የሆነ የቅድሚያ ክፍያ ይሰጣል። ልዩ የቅድሚያ የሥራ ክፍያ ለአንዳንድ አበል የሚያገኙ ወጣትና ተማሪዎች ሊሰጥ ይችላል።

አንዳንድ የሶስተኛ ደረጃ ተማሪዎች ከመኖሪያ ቤታቸው እስከ ት/ቤታቸው ለመጓጓዣ ወጪ እንዲሸፍን ለመርዳት **የመጓጓዣ ኣበል/ Fares Allowance** ይሰጣቸዋል።

**ለሶስተኛ ደረጃ ተማሮዎች ብድር፡** የፋይናንስ እርዳታ ብድር በፍላጎት የተመሰረተ አሰራር ሲሆን ለወጣትና ለተማሪ የሚከፈል አበል ሲሆን እንዲሁም ለሶስተኛ ደረጃ ተማሪዎችና አንዳንድ በወላጆቻቸው የገንዘብ ገቢ መጠን ምክንያት አበል ለሚወስዱ ይሆናል። ለአንዳንድ ማብራሪያ ሴንተርሊንክን ማናገር።

**የገቢ ምንጪ ባንክ/ Income Bank፡** የወጣትና የተማሪ አበል የሚያገኙ ተማሪዎች በሁለት ሳምንት ገደብ የሌለው የገቢ መጠን ሲያገኙ የገቢ ምንጪ ባንክ ይፈጠራል ማለት ነው። የተማሪዎች ገቢ መጠን [እስከ $6000 ዶላር] ሲኖራቸው ባንክ ይፈቅድላቸዋል እንዲሁም በእረፍት ጊዜ በሁለት ሳምንት ከዚህ የበለጠ ገቢ ከሆነ ክፍያው/አበሉን አይቀንስም ማለት ነው።

**የጤና መከላከያ ካርድ/ Health Care Card፡** ለአንዳንድ ሐኪም ለሚያዘው መድሃኒት በቅናሽ ዋጋ ለመግዛት ይቻላል። ለሥራ ፈላጊዎች፤ ለሙሉ ቀን ተማሪዎች በሚያቀርቡት የገቢ መጠን መሰረት ሲያመለክቱ በቀጥታ የጤና መከላከያ ካርድ ይሰጣቸዋል።

**ለመድሃኒት መግዣ የሚሆን አበል/ Pharmaceutical Allowance፡** ለወጣትና ተማሪ አበል የሚያገኙ እና የሚታመሙ ለጊዜው የገንዘብ አቅም ለሌላቸው ይሆናል።

## **የሴንተርሊንክ አገልግሎት ለወጣቶች**
[እንዲሁም የሴንተርሊንክ አበል ለሚያገኙ ሰዎች የሚሰጥ ይሆናል።]

**ለወጣት ቡድን** በሴንተርሊንክ ውስጥ ይገኛል እንዲሁም ስለ ትምህትና ስልጠና የሥራ አመራረጥ በማስረዳት የገንዘብ ገቢ ምንጪ የሚያገኙበትን መንገድ ከወጣቶቹ ጋር በመነጋገር የሚያስረዳ ኃላፊ ሠራተኛ እንደተመደበ ነው።

**ልዩ ለወጣቶች አገልግሎት የሚያቀርቡ ክፍሎች** ማለት የማሕበራዊ ሠራተኛና ሌሎችን ልዩ ሙያ ያላቸው ከዚሕ በታች ተካተዋል፡

- ቤት ለሌለው ወጣት እርዳታ የሚያቀርብ
- ቀደም ብሎ ት/ቤት ለማቋረጥ ላሰበ ወጣት ጣልቃ የመግባት
- እንክብካቤና ለሥራ የሚሆን ምክር ማቅረብ
- ወደሚመለከተው በመላክ መርዳት

**የሥራ ሙያ መረጃ ማእከላት** ሁሉንም የሙያ ኮርስ ዓይነት የሚያካተት መረጃ በነጻ በቀላሉ ማቅረብ። 12 ማእከላት የሚሆኑ በርእሰ ከተማዎች ይገኛሉ። አንድ ማእከል የራሱ የሆነ ትንሽ መጽሐፍና ቪዲዮ ሲኖረው እንዲሑም ለሥራ ማመልከቻ ለመጻፍና ለቃለ መጠይቅ እንዲዘጋጁ ለመርዳት በኮምፒተርና በመጻፍ እርዳታ ይቀርባል ።

በራስሕ ለመርዳት የሚያገለግሉ መሣሪያዎች በሁሉም የሴንተርሊንክ ጽ/ቤት ሲገኝ እነዚህም፡

- ለክፍት የሥራ ቦታ ዝርዝር የሚጫን ስክሪን
- ስልክ፣ ፎቶ ኮፒና ፋክስ
- ለሥራ ማመልከቻና የሕይወት ታሪክ ማዘጋጀት እንዲሁም የኮምፒተርና ኢንተርኔት አገልግሎት
- የሥራ መመሪያ፣ ጥራዝ ወረቀትና ማስታወሻ መጻፊያ ቦርድ

## **ለሴንተርሊንግ የሚደረግ ግዴታ**
በሴንተርሊን አበል የሚያገኙ ሰዎች ለሚያገኙት ክፍያ ሊቀይር የሚችል ነገር ካለ ለሴንተርሊንግ መንገር ግዴታ ይሆናል።

ወደ ውጭ አገር በመሄድ የሴንተርሊንክን ክፍያ ሊበክል ስለሚችል መናገር ኣስፈላጊ ነው። ን

ከሌሎች መንግሥታዊ ድርጅቶች ጋር ጥሬ መረጃዎችን ማመሳሰል፡ ሁልግዜ ለሴንተርሊንክ ትክክለኛ የሆነ መረጃ መስጠት አስፈላጊ ነው ምክንያቱም የቀረበው መረጃ ከሌሎች ምንግሥታዊ ድርጅቶችና ትምህርት ተቋማት ሳሰላል።

ከእንግሊዝኛ ሁለተኛ ቋንቋ በስተቀር በበለጠ ማብራሪያ ለማግኘት በስልክ 13 1202 መደወል ወይም "ተማሪዎችንና ወጣቶችን መርዳት"/ "Help for Young People and Students" የሚለውን በመረጃ ወረቀቱ ላይ [በ17 ቋንቋዎች] በሴንተርሊንክ ጽ/ቤት መጠየቅ ወይም ብዌብ ሳይት: http://www.centrelink.gov.au/internet/internet.nsf/multifilestores/yps0112 መጎብኘት ይሆናል።

# የበለጠ ማብራሪያ የሚገኝባቸው ምንጮች

## አጠቃላይ መረጃዎች

- ለሥራና ኮርስ ለማድረግ መዘጋጀት/ Job and Course Explorer (OZJAC), በአብዛኛው ት/ቤት ባሉ ቤተ መጻሕፍት በሚገኝ ኮምፒተር በበለጠ የትምህርት ሙያ የሚገኝበትን የመረጃ አገልግሎት ማግኘት። እንዲሁም የOZJAC ኮርስ መመሪያ አለው።
- በሥራ መምሪያ፣ የኮመንዌልዝ ትምህርት፣ ሳይንስና ስልጠና መምሪያ/ Commonwealth Department of Education, Science and Training (DEST) የወጣ ነው። ለዚህ መመሪያ ለማግኘት በት/ቤትህ ወይም በአካባቢ በሚገኘው ሴንተርሊንክ ማረጋገጥ።
- እንዲሁም ስለ ሶስተኛ ደረጃ ተቋም ባለ ትንሽ መጽሐፍ ማይት ነው።

## ለVCE/VCAL አጠቃላይ መረጃ

መረጃ ማነቀረቢያ ክፍል/Information Section
Victorian Curriculum Assessment Authority
41 St Andrew Place
EAST MELBOURNE 3002
Phone: (03) 9651 4300 Fax: (03) 9651 4324
Website: www.vcaa.vic.edu.au

## ስለ የርቀት ትምህርት መረጃ

Distance Education Centre Victoria
315 Clarendon Street
THORNBURY VIC 3071
Phone: (03) 8480 0000 Fax: (03) 9416 8493
Website: www.distance.vic.edu.au

## ለወላጆች አጠቃላይ የትምህርት መረጃ

በትምህርትና ስልጠና መምሪያ የተዘጋጀ "A-Z ለወላጆች መመሪያ፡ በቪክቶሪያ መንግስቲ ት/ቤት የጥናት አመለካከት"/"A-Z Guide for Parents: Education in Victorian Government Schools at a glance" [ከእንግሊዝኛ ባሻገር በ12 ቋንቋዎች የተተረጎመ]፡ ዌብ ሳይት: www.sofweb.vic.edu.au/lem/esl/azguide.htm

ለበለጠ ማብራሪያ በት/ ቤት የ ESL ፕሮግራም ወይም መረጃዎች በ14 ቋንቋዎች የተተረጎመ ዌብ ሳይት: www.sofweb.vic.edu.au/lem/esl/index.htm

## ስለ TAFE መረጃ

የስልጠናና ሶስተኛ ደረጃ ትምህርት ጽ/ቤት (OTTE)
2 Treasury Place
EAST MELBOURNE VIC 3002
Phone: (03) 9637 2000 Fax: (03) 9637 2470

ዌብ ሳይት: www.otte.vic.gov.au
የTAFE መስመር፡ 131823

## ስለ ሥራ፣ TAFE እንዲሁም ዩኒቨርሲቲ መረጃ ለማግኘት

Melbourne Career Information Centre
1st Floor, 176 Bridge Road
Richmond 3121
Phone: (03) 9299 1038 Fax: (03) 9299 1099